# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር አፈጻጸምን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት






ጥር 2008 ዓ.ም

ደብረ ዘይት

## ማውጫ


**ክፍል አንድ** ..... **1**

መግቢያ ..... 1

የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የፋይናንስ ምንጭ ..... 3

የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሥልጣን እና ተግባራት ..... 4

የአሰራር ሥርዓት መግለጫ ..... 7

የኦዲቱ ዓላማ ..... 7

የኦዲቱ አከባቢ ..... 7

የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች ..... 8

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርት ..... 9

የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ ..... 10

**ክፍል ሁለት** ..... **11**

የኦዲት ግኝቶች ..... 11

ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና ጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ ..... 11

በሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበር ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርት ድጋፍ መሰጠቱን በተመለከተ ..... 15

በሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍ የምርምር ሥራ መከናወኑን እና ቴክኖሎጂዎች ተሰራጭተው መተግበራቸውን በተመለከተ ..... 16

የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ያካተተ ስለመሆኑ ..... 19

የኢንስቲትዩቱ ንብረቶች/መሳሪያዎች እና ኬሚካሎች ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ ..... 20

ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ሎጅስቲክስ አመራርና ግብይት ዙሪያ ለማቀነባበሪያዎቹ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ ..... 21

የሥጋ፣ ወተትና መኖ ግብዓት አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን መደረጉን በተመለከተ ..... 24

ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መሰራቱን በተመለከተ ..... 26

በሥጋና ወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ተወዳዳሪ በመሆን ለአገር ውስጥና ለውጭ ሀገር በበቂ ሁኔታ ምርቶችን የሚያቀርቡ ስለመሆኑ ..... 29

ኢንስቲትዩቱ ሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ማድረጉን በተመለከተ ..... 32

በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ዙሪያ መልካም ተሞክሮዎች ተቀናብረው ተግባራዊ የተደረጉ ስለመሆኑ ..... 34

ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተደራጁና ለሚመለከተው አካል የተሰራጩ መሆኑን በተመለከተ ..... 36

ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት መዳረሻ ገበያ እስኪደርስ ድረስ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ለቁራዎች ግብረ መልስ በመስጠት አፈጻጸሙን ያሳደገ መሆኑን በተመለከተ ..... 37

ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር ላይ ተሳትፈው ውጤት ያላስመዘገቡ ኢንዱስትሪዎችን በመለየት የኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረጉን በተመለከተ ..... 39

በኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ውጤታማነትን በተመለከተ ..... 41

በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን በመስክ በመከታተል የአፈጻጸም ሪፖርት መቅረቡን በተመለከተ ..... 42

ኢንስቲትዩቱ የአማካሪ ም/ቤት መቋቋሙን በተመለከተ ..... 43

**ክፍል ሶስት ..... 45**

የመደምደሚያ ሃሳቦች ..... 45

**ክፍል አራት ..... 61**

የማሻሻያ ሃሳቦች ..... 61

**አባሪዎች ..... 66**

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ..... አባሪ 1

የአሰራር ሥርዓት መግለጫ ..... አባሪ 2

በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ የቀረበላቸው እና በመስክ የታዩ ቦታዎች ዝርዝር ..... አባሪ 3

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የእንስሳት ሀብት ልማት ዘርፍ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ፣ ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት በማገልገል፣ የውጪ ምንዛሬ በማስገኘት እና የውጪ ምርቶችን በመተካት ረገድ ከፍተኛ ሀገራዊ ጠቀሜታ እንዳለው የሚታወቅ ሲሆን ከእንስሳት ሀብታችን ተገቢውን ጠቀሜታ ለማግኘትና ምርትና ምርታማነትን በአግባቡ ማሳደግ እንዳይቻል እንቅፋት የሆኑት ዋነኛ ምክንያቶች ውስጥ ባህላዊ የእንስሳት አረባብ ዘዴ፣ የመኖ በብዛትና በጥራት ያለመኖር፣ በቂ የእንስሳት ጤና አገልግሎት አለመሟላት እና ዘመናዊ የግብይት ስርዓት አለመኖር ናቸው፡፡

2. ከእንስሳት ሀብታችን የተሻለ ምርትና ገቢ ለማግኘት እንዲቻል በህብረተሰቡ ዘንድ የተጠናከሩ ጥረቶች በመደረግ ላይ ሲሆኑ መንግስትም በሥጋና ወተት ምርትና አቅርቦት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን አቅም ለመገንባት እና የሥጋና የወተት ምርትና አቅርቦት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 143/2000 ዓ.ም በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር አቋቋመ፡፡ በ2002 ዓ.ም ኢንስቲትዩቱ በሥጋና ወተት ማምረት፣ አቅርቦት፣ ማቀነባበር እና ግብይት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላትን አቅም ለመገንባት፣ የሥጋና የወተት ምርትና አቅርቦት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል፣ በመስኩ ባለሃብቶች እንዲሳተፉ በማበረታታት ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት እና ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟሉ እንስሳትና የእንስሳት ምርቶች ለውጭና ለአገር ውስጥ ገበያ በአይነትና በብዛት የሚቀርብበትን ሁኔታ ማመቻቸት ለማስቻል ተጠሪነቱ ለግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሆኖ በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 176/2002 በማሻሻያ ተቋቁሟል፡፡ ይህ ዘርፍ እንዲጠናከርና የግል ባለሃብቱም በቴክኖለጂ የተደገፈ አሰራር በማስፋፋት በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶችን ማቅረብ እንዲቻል የአቅም ግንባታ፣ የገበያ ማስፋፋትና የኢንቨስትመንት ድጋፎችን ለባለሃብቱ እንዲሰጥ ለማድረግ የኢትዮጵያ ስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ተጠሪነቱ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሆኖ በደንብ ቁጥር 295/2005 ዓ.ም በድጋሚ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በዚሁ

ደንብ ውስጥ ኢንስቲትዩቱን የሚያማክር የአማካሪ ምክር ቤት እንዲመሰረትና ምክር ቤቱም ሰብሳቢና አግባብ ካላቸው የመንግሥት መ/ቤቶችና ከግሉ ዘርፍ ጭምር የተውጣጡ በመንግሥት የሚሰየሙ አባላት እንዲኖሩትና እንዲቋቋም በአንቀጽ 8/1 ተፈቅዶለታል፡፡

3. አገራችን ከፍተኛ የእንስሳት ሃብት ያላት ስትሆን 53.4 ሚሊዮን የቀንድ ከብት፣ 25 ሚሊዮን በጎች፣ 22.78 ሚሊዮን ፍየሎች እና 49.3 ሚሊዮን ዶሮዎች እንዲሁም 4.9 ሚሊዮን የባህላዊ፣ 41,687 የሽግግርና 144,258 የዘመናዊ ቀፎዎች እንዳላት በCSA (Central Statistics Authority), 2010/2011 እ.ኤ.አ መረጃ ያስረዳል፡፡
ነገር ግን ከዚህ የእንስሳት ሃብት የሚገኘው ምርትና ምርታማነትም በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ሃገሪቱ 10.7 ሚሊዮን የወተት ላሞችና 7.4 ታላቢ ላሞች ሲኖራት 4.06 ቢሊዮን ሊትር ወተት እንዲሁም 49.3 ሚሊዮን ዶሮዎች 98.3 ሚሊዮን እንቁላልና 60 ሺህ ቶን ሥጋ የተመረተ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም በ5.13 ሚሊዮን ቀፎዎች ውስጥ ከሚገኙ 10 ሚሊዮን ህብረ ንቦች 53.86 ሚሊዮን ኪ.ግ ማር ሲገኝ በሃገራችን ውስጥ ከሚገኙ የውሃ አካላት ማለትም ከግድቦች፣ ሃይቆችና ኩሬዎች በዓመት ከ15,417-17,308 ቶን የዓሳ ሥጋ እንደተመረተ በዚሁ ዓመት የተገኘው መረጃ ያስረዳል፡፡

4. ከእንስሳት የሚገኘው ምርትና ምርታማነት አናሳ ከመሆኑ የተነሳ የሃገራችን የነፍስ ወከፍ ፍጆታ ዝቅተኛ ነው፡፡ በአፍሪካ ሀገሮች የዳልጋ ከብት ሥጋ ፍጆታ 23 ኪ.ግ፣ የወተት ፍጆታ 27.5 ሊትር፣ ሲሆን የኛ አገር የዳልጋ ከብት ስጋ ፍጆታ 9 ኪ.ግ፣ የወተት 19 ኪ.ግ፣ የእንቁላል 1.2፣ የዶሮ ሥጋ 1ኪ.ግ፣ የዳልጋ ከብት ሥጋ ምርታማነት (Dressing percentage) ከ35-40 % ነው፡፡ ከበግና ፍየል የሚገኘው አማካይ የሥጋ ምርት መጠን በቅደም ተከተል ሲቀመጥ 10 እና 9 ኪ.ግ ሲሆን የመስራቅ አፍሪካ አገሮች ግን ከበግ በአማካይ 13.5 ኪሎግራም ከፍየል 13.1 ኪሎግራም ሥጋ ያገኛሉ፡፡

5. በመሆኑም ይህ የእንስሳት እና የእንስሳት ተዋጽኦ ዘርፍን ውጤታማ ለማድረግ ጉልህ ሚና ያለው የስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መንግስት የሰጠውን

ተግባርና ኃላፊነትን በተቀላጠፈ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን በማጣራት በአሰራር ሂደት የተገኙ ክፍተቶችን በመለየት ለኢንስቲትዩቱ የማሻሻያ ኃሳብ በመስጠት ኢንስቲትዩቱ ወደፊት የሚያከናውናቸው ተግባራት የተቀላጠፈ እና ውጤታማ እንዲሆን የክዋኔ ኦዲት ማከናወኑ ጠቃሚ ነው፡፡

## የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የፋይናንስ ምንጭ

6. የስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የፋይናንስ ምንጭ ከመንግሥት ግምጃ ቤት የሚመደብ እና ከውስጥ ገቢ የሚሰበሰብ ሲሆን በ2005፣ በ2006 እና በ2007 በጀት ዓመታት ከማዕከላዊ ግምጃ ቤት እና ውስጥ ገቢ በጀት አፈጻጸም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| | ከማዕከላዊ ግምጃ ቤት የተመደበ በጀት በብር | | | አፈጻጸም በብር | | | አፈጻጸም በመቶኛ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | 2007 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | 2007 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም % | 2006 ዓ.ም % | 2007 ዓ.ም % |
| | 11,064,250 | 13,876,493 | 19,809,610 | 9,297,906.75 | 12,943,301.71 | 18,742,888.92 | 84 | 94 | 94.6 |
| | ከውስጥ ገቢ የተመደበ በጀት በብር | | | አፈጻጸም በብር | | | አፈጻጸም በመቶኛ | | |
| | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | 2007 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | 2007 ዓ.ም | 2005 ዓ.ም % | 2006 ዓ.ም % | 2007 ዓ.ም % |
| | 1,249,000 | 1,300,000 | 1,495,000 | 1,214,997.84 | 1,274,962.35 | 1,066,721.08 | 97.3 | 98 | 71.4 |
| ድምር | 12,313,250 | 15,176,490 | 21,304,610 | 10,512,904.6 | 14,218,294.06 | 19,809,610.00 | 85.4 | 94 | 92.9 |

## የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሥልጣን እና ተግባራት

7. የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የተቋቋመበትን ዓላማ እና ራዕይ ለማሳካት የሚያስችሉ ሥልጣንና ተግባራት አሉት፡፡ እነርሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡
    1. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚረዱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችን፣ መመሪያዎችንና መርሐ ግብሮችን ማዘጋጀት፤ ሲፈቀዱም ተግባራዊ ማድረግ፤
    2. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርፀት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች በማሸጋገር ገበያ ውስጥ እንዲገቡ መደገፍ፤ እንዲሁም ኢንዱስትሪዎቹ የምርምርና ሥርፀት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ መደገፍ፤
    3. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪን ለማስደግ የሚያግዙ የገበያ ጥናትን ጨምሮ ሌሎች የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ማከናወን፣ የኢንዱስትሪ ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲሁም በዓለም ገበያ ለማስተዋወቅ ድጋፍ መስጠት፣ ውጤታማ የግብይት ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፤
    4. ለሥጋና ወተት ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያና ሌሎች መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀትና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት፤
    5. ለሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት፣ የናሙና ምርት ማምረቻና ላብራቶሪዎች በማቋቋም መደገፍ፣ ለሚያመርቷቸው ምርቶች ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የፍተሻ አገልግሎት መስጠት፤ ኢንዱስትሪው የፍተሻ ላብራቶሪዎች እንዲያቋቁም ማበረታታትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ሠርተፊኬሽን እንዲያገኙ ማስቻል፤
    6. የእንስሳት ሀብትና ኢንዱስትሪውን አስመልክቶ ባሉት የኢንቨስትመንት አማራጮች ላይ የደሰሳ ጥናት በማድረግ የመረጃ ቋት መመስረት፤ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ መተንተን፣ ማደራጀት፣ በየጊዜው

እየተገመገሙ ወቅታዊ እንዲሆኑ ማድረግ እና እንደ አስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎች ማሠራጨት፤

7. ለእንስሳት ገበያ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ-ልማቶች እንዲስፋፉ እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የእንስሳት ምርት የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ፋሲሊቲዎች እንዲሟሉና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ክትትል ማድረግ፤
8. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ማዘጋጀትና ማሰራጨት፤ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች ጠቋሚ ጥናት ማድረግ፤ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል ማድረግና በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሔ መስጠት፤ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ማካሄድና በንዑስ ዘርፉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማነቆዎች ኢንዲወገዱ ድጋፍ መስጠት፤
9. በሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ለሚሠማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መስጠት፤
10. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ዘርፍን ልማት የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን መስጠት፣ በዚህ ረገድ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋርም በመተባበር የዘርፉን የሰው ኃይል ማብቃት፤
11. በዓለም አቀፍ ደረጃ ብቃትን ጠብቆ ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ እንዲቻል በቁርኝት መርሐ ግብር የአቅም ግንባታ ማከናወን፤ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት፤
12. ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር የምርትና የሰው ኃይል ልማትን በተመለከተ በመተባበር መሥራት፣ በጋራ የምርምር ሥራዎችን ማካሄድ፣ በዘርፉ የአገር ውስጥ የምርምር አቅም እንዲጠናከርና ኢንዱስትሪዎቹ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር ትስስር እንዲኖራቸው ማገዝ፤ የዘርፉን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት፤
13. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪውን ልማት ሊያፋጥኑና ተወዳዳሪ ሊያደርጉ የሚችሉ የዓለም አቀፍ የምርጥ ተሞክሮዎች ጥናት ማካሄድና የሚቀመሩትን ተሞክሮዎች ተግባራዊ ለማድረግ ለአንዱስትሪዎቹ ድጋፍ መስጠት፤

14. ለዘርፉ የግብዓቶች አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት እንዱስትሪዎች እንዲለሙ መደገፍ፤ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ በምርቶች እሴት ሰንሰለት በዘርፉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤ በተለይም በዘርፉ የተሰማሩ የጥቃቅን እና አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከመካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር ውጤታማ የምርት፣ የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖራቸው መደገፍ፤
15. የአገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በዘርፉ ላይ ለመሰማራት እንዲነሳሱ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ዞኖች እንዲለሙ ማበረታታት፤ በኢንዱስትሪ ዞኖች ውስጥ የሚሰሩ ባለሀብቶችን መደገፍ፤
16. በዘርፉ አዳዲስና ተወዳዳሪ ባለሀብቶችን ለመፍጠር ኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ፕሮግራም መዘርጋትና የኢንኩቤሽን ማዕከላት ማቋቋም፤
17. በዘርፉ በጥናትና ምርምር የሚገኙ ውጤቶች የፈጠራ ባለቤትነት መብት እንዲጠበቅላቸው ድጋፍ መስጠት፤
18. በድኅረ -ምርት የሚያጋጥሙ የምርት ብክነቶችን ለመቀነስ ድኅረ ምርት ቴክኖሎጂዎች፣ የማቅዘቀዣ ሰንሰለቶች፣ ዘመናዊ መጋዘኖች፣ ዘመናዊ ትራንስፖርትና ሌሎች አስፈላጊ የሎጅስቲክስ መሠረተ-ልማቶች እንዲስፋፉ መደገፍ፤
19. የሥጋና ወተት አምራች ኢንዱስትሪዎች ማህበራት ለዘርፉ ንግድና ኢንቨስትመንት ዕድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና እንዲጫወቱ የአቅም ግንባታ ድጋፎች መስጠት፤
20. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን እንዲጠቀምና የአከባቢ ብክለት እንዳያስከትል ድጋፍ መስጠት፤
21. ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች መንግስት በሚወስን ተመን መሰረት አገልግሎት ዋጋ የማስከፈል፤
22. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል መዋዋል፣ በራሱ ስም መክሰስና መከሰስ፤
23. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማች ተግባራትን ማከናወን ናቸው፡፡

## የአሰራር ሥርዓት መግለጫ (System description)

8. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከወቅታዊ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት አንገብጋቢ ችግሮች እንዲሁም የመንግስትን እስትራቴጂ መሰረት አድርጎ ምርምር በማከናወን ለኢንዱስትሪዎች የሚያቀርብ እና ለኢንዱስትሪዎች በዘርፉ በሚያጋጥሙዋቸው ችግሮች ዙሪያ ሁለገብ ድጋፍ (የምክር አገልግሎት፣ የክህሎት ክፍተትን በመለየት ሥልጠና የመስጠት፣ በዘርፉ ከተሠማሩ ተቋማት ጋር ቁርኝት የመፍጠር፣ አገልግሎቶችና የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ፓኬጆችን ለተገልጋይ ተደራሽ የማድረግ) ተግባራትን የሚያከናውን ሲሆን አጠቃላይ የኢንስቲትዩቱ ዝርዝር የአሰራር ሥርዓት መግለጫው በአባሪ 2 ተያይዞ ቀርቧል፡፡

### የኦዲቱ ዓላማ ፡-

9. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የሚያከናውናቸው የድገፍ አገልግሎቶች እና የቴክኖሎጂዎች ሽግግር ቀልጣፋ፣ ግልጽነት፣ ተጠያቂነት የተላበሰና በዘርፉ የወጡትን ህግና ደንቦችን መሠረት ያደረገ ፣ ሥርዓት የተከተለ እና ኢንስቲትዩቱ በእንስሳትና እንስሳት ተዋጽኦ ምርት፣ ማቀነባበርና ግብይት ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶችና ማህበራትን አቅም መገንባቱን፣ ኢንቨስትመንትና ገበያ እንዲስፋፋና እንዲቀላጠፍ በመደገፍ ደረጃውን የጠበቁና ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶችን ለውጭ ገበያ በብዛትና በጥራት እንዲያቀርቡ ማደረጉን ለማረጋገጥ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከሰቱ የአሰራር ችግሮች ካሉ በመለየት የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነትን ማጠናከር ነው፡፡

### የኦዲት አካባቢ፡-

10. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Potential Audit Area) የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ሽግግር አፈጻጸም ቀልጣፋ፣ ኢኮኖሚያዊና ስኬታማ በሆነ መንገድ እየተከናወነ መሆኑን እና ለዚሁ ተግባር የዋለው ግብዓት ያስገኘውን ተመጣጣኝ ውጤት (Value for Money) ማረጋገጥ ነው፡፡

### የኦዲቱ ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች፡-

11. የኦዲት ቡድኑ በደሰሳ ኦዲት ወቅት ለለየው ኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area) 3 (ሶስት) የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን ያስቀመጠ ሲሆን፣ በመጀመሪያው የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ ስር ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫዎችን አስቀምጧል፡፡ እነርሱም፡-

1. በሥጋና በወተት ኢንዱስትሪ ልማት ሥራ ላይ ለተሰማሩ አካላት መልማት የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርፀት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች በማሸጋገር ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ ምርት ማምረት እንዲችሉ እገዛ መደረጉን እንዲሁም ምርቶቹን ለአገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ እንዲቻል የገበያ ጥናቶችን በማከናወን፣ በማስተዋወቅና በማስተሳሰር ድጋፍና ክትትል መደረጉን ማረጋገጥ፤
   - 1.1 በሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ሥራ ላይ ለተሰማሩ አካላት መልማት የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች በምርምርና ሥርፀት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎቹ እንዲሸጋገሩ ድጋፍ የተሰጠ መሆኑን መገምገም፤
   - 1.2 ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የእንስሳት ምርቶች ለውጭና ለአገር ውስጥ ገበያ በዓይነት፣ በጥራትና በብዛት ለማቅረብ የሚያስችሉ የገበያ ጥናቶች በማከናወን የማስተዋወቅና የማስተሳሰር ሥራ መሰራቱን ማረጋገጥ፤
2. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ላይ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎች መዘጋጀቱን፣ የደሰሳ ጥናት በማድረግና የመረጃ ቋት በመመስረት፣ መረጃዎችን በየጊዜው እየገመገሙ ወቅታዊ በማድረግ መረጃዎቹን ለሚፈልጉና ለሚመለከታቸው አካላት መሰራጨቱንና ተደራሽ የመረጃ ሥርዓት መመስረቱን እንዲሁም በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል መደረጉን መገምገም፤
3. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የድጋፍ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን መገምገም እንዲሁም ዘርፉን የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች

እንደአስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን በመስጠት ድጋፍ መደረጉን ማረጋገጥ፤

የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት፡-

12. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች (audit issues) 46 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (evaluative critera) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መሰረት የሆኑት የኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ የሚ/ሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 295/2005 ዓ.ም፣ የሥጋ ተረፈ ምርት አሰባሰብ ሥርዓት ለመፍጠር የተዘጋጀ ሰነድ፤ ከኦሮሚያ፣ አማራ፣ ትግራይና ሶማሌ ክልል የእስልምና ጉዳዮች ም/ቤት ጋር በመሆን የሃላል ዕርድ ሥርዓትን በኤክስፖርት ቄራዎች ለማጠናከር የተዘጋጀ ዕቅድ ህዳር 2006 ዓ.ም፣ በኢንስቲትዩቱ ለእንስሳት ሃብት ልማት ኢንቨስትመንት የሚውሉ መሬቶች ለመለየት በክልሎች የተደረገ ጥናት የመስክ መልስ ሪፖርት 2004 ዓ.ም፤ የኢንቨስትመንትና ገበያ ማስፋፊያ ዳይሬክቶሬት የድጋፍ ዕቅድ ሰኔ 2007 ዓ.ም፤ በኢንዱስትሪ ሚ/ር የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ዕቅድ ጥናት ሪፖርት መጋቢት 2006 ዓ.ም፤ በኢንዱስትሪ ሚ/ር የኢትዮጵያ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የ2006 በጀት ዓመት የድጋፍ ዕቅድ ሐምሌ 2006 ዓ.ም ፤የ2005 ዓ.ም በጀት ዓመት ዓመታዊ ዕቅድ ዝርዝር የሥራ መርሃ-ግብር፤ የ2007 ዓ.ም የውጤት ተኮር ሥርዓት ዕቅድ፤የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የ2006 በጀት ዓመት የድጋፍ ዕቅድ እና የመልካም ተሞክሮዎችን በማካተት የተዘጋጀ ነው፡፡ በተዘጋጁትም የመመዘኛ መስፈርቶች ላይ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት የበላይ ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተሰጥቷቸው አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር በአባሪ 1 ተያይዞዋል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ :-

13. የክዋኔ ኦዲቱ የሸፍነው ከ2005 እስከ 2008 በጀት ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ የስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥና የቴክኖሎጂ ልማት ሽግግር አፈጻጸም ወጪ ቆጣቢ፣ ብቃት ያለውና ውጤታማ መሆኑን ላይ ሆኖ የክዋኔ ኦዲቱ

ኢንስቲትዩቱ ድጋፍ እየሰጣቸው ባሉ በናሙና በተመረጡ 4 (ሃሽም/ሂልሜክስ፣ ሉና፣ ኤልፎራ እና ጅጅጋ ላይቭስቶክ) የሥጋ እና 6 (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ኤሌምቱ እና ያቅላ) የወተት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች፣ ሁለት የመኖ ማቀነባበሪያዎች (አለማ ካዋዳይስ እና አዲስ ሞጆ) እና ሶስት(የሉሜ፣ ሃዋሳ እና ጅግጅጋ) የክልል ከተማ ኢንዱስትሪ ልማት የሥራ ሂደቶች ላይ ነው፡፡ ዝርዝራቸውም **በአባሪ 3** ተያይዞ ቀርቧል፡፡ኦዲቱም የተከናወነው ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የኢንዱስትሪዎቹን እና መ/ቤቶቹን  የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በቼክ ሊስት በመወያየት እና በማጣራት፣ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ሥርዓትን ለመስፈጸም ሥራ ላይ የዋሉ የተለያዩ ዶክመንቶችን በመከለስ እና አሰራሩን በአካል ተገኝቶ በመገምገም ነው፡፡

## ክፍል ሁለት

## የኦዲቱ ግኝቶች

### ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና ጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፡-

14. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች የምርት ሂደት፣ ምርት ዕቅድና ጥራት ቁጥጥር በማድረግ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟላ ምርት ለሃገር ውስጥና ለዓለም ገበያ እንዲያቀርቡ ሊደግፍ ይገባል፡፡

15. ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ውጤት ማስመዝገብ አለመቻሉን በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሥጋ (ሃሽም/ሄልሜክስ፣ ኤልፎራ እና ሉና ቄራዎች)፣ ወተት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ ኤሊምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) እና መኖ (አዲስ ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) ማቀነባበሪያዎች በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ እና በኢንስቲትዩቱ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

16. ለአብነት ያህል ሃሽም እና ሉና ከሁለት ዓመት በፊት እንዲሁም በመስከረም 2008 ዓ.ም አጠቃላይ በሃገሪቱ የሚገኙ የኤክስፖርት ቄራዎች በጥራት ምክንያት በሶስት ዙር ከሰባት ኤክስፖርት ቄራዎች የቀረበ 270 ቶን (1.59 ሚሊዮን ዶላር) ሥጋ በመበላሸቱ ለ6 ቀናት ከገበያ የታገዱ ሲሆን ኢንስቲትዩቱ በቅድመ ምርት፣ በምርት ሂደትና ድህረ ምርት ሰኒቴሽንና ሃይጅን ላይ በተከታታይ ድገፍ በማድረግ የሥጋ ምርት ንጽህናው በተጠበቀ ሁኔታ እንዲመረት ሊያደርግ አለመቻሉን፣ ጥራቱን የጠበቀ ሥጋ መዳረሻ እስኪደርስ ድረስ በሰንሰለቱ ውስጥ ክትትል በማድረግ ለቄራዎች ግብረ መልስ በመስጠት ማስተካከያ እርምጃዎችን እንዲተገብሩት የሚያስችላቸው ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን ፣ ወተትና የወተት ውጤቶች

የጥራት ደረጃ አጠባበቅ ሕግ፣ ደንብና መመሪያ እንዲኖር እና ሥራ ላይ እንዲውል ክትትል አለመደረጉን ፣ ከወተት ማቀነባበሪያዎች የምርት ናሙና በማሰባሰብ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ኬሚካላዊና ማይክሮባዮሎጂካዊ ጥራት ፍተሻ በማድረግ ማቀነባበሪያዎቹ እንዲያሻሽሉ ድጋፍ አለመሰጠቱን እና በመኖ ምርቶች ላይ የላብራቶሪ ትንተና እንዲደረግባቸው ኢንስቲትዩቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት አለመሥራቱን በኢንስቲትዩቱ ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎች በኦዲቱ ወቅት ከቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

17. በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ በምርት ሂደት የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ቀርበው እገዛ ያላደረጉ ሲሆን ባለሙያዎቹ ወደ ኢንዱስትሪዎቹ በሚሄዱበት ወቅት ስለ ምርት ሂደቱ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በጥያቄ ስለሚያባክኑ ማቀነባበሪያዎቹ ለባለሙያዎች ያላቸው ሙያዊ አመለካከት በመቀየሩ ሙያተኞቹን ለማስተናገድ አለመቻላቸውን እና በምርት ዕቅድ ላይ አብሮ አለማቀድ እና የኢንስቲትዩቱ ድርሻ ምን እንደሆነ በዕቅዳቸው ላይ የማይገለጽ እና የማይታወቅ መሆኑን፣ ለዕርድ ወደ ቄራ የሚመጡ እንስሳት ከተሰበሰቡበት አከባቢ ተነስተው ለረጅም ጊዜ ያለ እረፍት የሚጓዙበት ሁኔታ በእንስሳት ምርት ላይ የጥራት ችግር እያስከተለ ስለሆነ ከተሰበሰቡበት አከባቢ ተነስተው ለስምንት ሰዓት ከተጓዙ በኋላ ማረፊያ ሊሆናቸው የሚችል ቦታ (holding areas) በቂ የመመገቢያና ውሃ መጠጫ ገንዳዎች አለመሟላታቸውን እንዲሁም ከጥራት ጋር በተያያዘ የሥጋና ወተት ላብራቶሪዎች የተለየ ክፍል የሌላቸው ፣ያረጁና ጥገና ያልተደረገላቸው እና በትክክል ስለመስራታቸው ማረጋገጫ (Calibration test) የሌላቸው መሆኑ፣ በቂ የላብራቶሪ ፋሲሊቲ (ይህም፡- የተለየ የላብራቶሪ ክፍል፣ ኤር ኮንዲሽነር፣ ፋኖች እና ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች…)፣ የላብራቶሪ ማስኬጃ መመሪያ ወይም ማንዋል የሌላቸው፣ የላብራቶሪ ቆሻሻ መቆጣጠሪያ (residue monitoring) መሳሪያ አለመኖር፣ ላብራቶሪዎቹ የኬሚካል እና ሪኤጀንት እጥረት ያለባቸው በመሆኑ ጊዜያቸው ባለፉ

ኬሚካልና ሪኤጀንቶች የሚጠቀሙበት ሁኔታ መኖሩን እና ኢንስቲትዩቱም ሞዴል ሰርቶ ማሳያዎች እና ላብራቶሪዎችን በማቋቋም በዚሁ መሰረት እንዲስፋፉ አለማድረጉን ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች በኦዲቱ ወቅት ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና በመስክ በተደረገ ምልከታ ለመረዳት ተችሏል፡፡

18. በተጨማሪም የወተት ማቀነባበሪያዎቹ የሰለጠነ የላብራቶሪ ባለሙያ እና መሳሪያዎች የሌላቸው በመሆኑ የማይክሮባይሎጂካል፣ አፍላቶክሲን እና ኬሚካል አናሊስስ የማያከናውኑ እና አቅራቢዎች ለወተት ባልተዘጋጀ እና ንጽህና በሌለው ዕቃ የሚያቀርቡ፣ ማቀነባበሪያዎቹ እና አቅራቢዎች ለወተት ሥራ በተዘጋጀ ተሽከርካሪ ሌሎች ዕቃዎችን የሚያጓጉዙ መሆኑን፣ ወተት ከረጅም ርቀት በማጓጓዝ የሚመጣበት ሁኔታ መኖሩን፣ የወተት ማቀነባበሪያዎች የወተት ማሰባሰቢያና ማቀዝቀዥያ ማዕከል እንዲያቋቁሙ ድጋፍ አለመደረጉን እና የተለየ ንጽህናውን የጠበቀ የወተት መረከቢያና መሸጫ ቦታዎች የሌላቸው መሆኑን በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ወቅት ከታዩ ስድስት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ጀኔሲስ ፋርም፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) ማቀነባበሪያዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

19. ስለ ሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ ጥራትን ለመቆጣጠር ከግብርና ሚ/ር ጋር ተሳስሮ መስራት ቢያስፈልግም ያለው ቅንጅት ደካማ መሆኑን እና አቅርቦት (Supply Chain) ላይ ትኩረት ተደረጎ አለመሰራቱን፣ ኢንስቲትዩቱ ቀጥታ ወደ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ትኩረት አድርጎ ሲሸጋገር ይዞ የመጣው ባለሙያ በግብርና (Production) ሙያ ላይ ይሰሩ የነበሩ በመሆኑ ማቀነባበሪያዎችን (Processing) ላይ ሊደግፉ የሚያስችላቸው ሙያ የሌላቸው መሆኑን፣ በኢንስቲትዩቱ የተሟላ ባለሙያ አለመኖሩን፣ የወተት ጥራትን በተመለከተ የወተት ጥራት አጠባበቅ ላይ ህግ ባለመኖሩ ችግሩ መፈጠሩን እና የወተት ፋብሪካዎች በየክልሉ የተበታተኑ በመሆኑ የቦታ ርቀት፣ የባለሙያ እጥረት መኖሩን እና አበል በቂ

አለመሆኑን፣ ኢንዱስትሪዎቹ በራሳቸው የእድሳት ችግር እና የቁጥጥር መላላት፣ የገኘ ሀገራት ተቆጣጣሪ አካላት በድንገት አይተው እንዲዘጋ በመወሳናቸው እና ገኘው በአረፋ በዓል ወቅት አውሮፕላን ውስጥ ያለው ቅዝቃዜ ይበቃል የሚል ኃሳብ በማቅረቡ ሥጋው በቁራው ማቀዝቀዣ ውስጥ መቆየት የሚገባውን ሰዓት ያህል እንዳይቆይ ገኘዎችና ላኪዎቹ በመስማማታቸው ምክንያት ሥጋው ተገቢውን ቅዝቃዜ ባለማግኘቱ መዳረሻ ላይ ሲደርስ በመበላሸቱ በአረብ ሀገራት እግዶች መጣላቸውን፣ መኖን አስመልክቶ ኢንስቲትዩቱ የራሱ የሆነ ላብራቶሪ የሌለው በመሆኑ ትንተና መስራት አለመቻሉን እንዲሁም ለወደፊት የጋራ በምግብና የመደሃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን (FMHAKA) ሥራ ጥምር ኮሚቴ በመጠቀም በጥራት ላይ የተመሰረተ የወተት ግብይት ህግ ለማውጣት የሚሰራ መሆኑን፣ መኖን አስመልክቶ አሁን ግን ከACDI/VOCA ጋር በመሆን አጠቃላይ የላብራቶሪ ትንተና ለመሥራት በሂደት ላይ የሚገኙ መሆኑን እና ኢንስቲትዩቱ በቅርቡ ወደ ኢንዱስትሪው የገባ በመሆኑ ፋሲሊቲዎች በሂደት እንደሚሟሉ የሚጠብቅ ሲሆን እስከዚያው በኢንዱስትሪ ዩኒቨርሲቲ ትስስር ያሉ ፋሲሊቲዎችን በጋራ ለመጠቀም በመሥራት ላይ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ አጠቃላይ የኢንስቲትዩቱን ላብራቶሪ ህንጻ ለመገንባት ዲዛይን በውጭ ኮንሰልታንት እንዲጠና በማድረግ የ300 ሚሊዮን የበጀት ጥያቄ ለጠቅላይ ሚ/ሩ የቀረበ ሲሆን በጀቱ ተፈቅዶ በቀጣይ አስፋላጊ የሆኑት የላብራቶሪ ህንጻዎችን እንዲገነቡ በማድረግ አሁን ካለው አፈጻጸም የተሻለ ለማስመዝገብ አስፈላጊውን ጥረት የሚያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

20. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና ጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍ አለመስጠቱ፣ ማቀነባበሪያዎቹ ጥራት የሌለው ምርት ለተጠቃሚው እንዲያቀርቡ በማድረግ ጥራቱና ደህንነቱ ያልተረጋገጠ የዓለም አቀፍ መስፈርትን ያላሟላ ምርት ለሃገር ውስጥና ለዓለም ገበያ በማቅረብ የኢንዱስትሪዎቹ ምርት ተወዳዳሪ እንዳይሆን በማድረግ ለኪሳራ እንዲዳረጉ ከማደረጉም በላይ በተጠቃሚዎች ላይ የጤና

ጉዳት እንዲደርስ ያደርጋል፤ እንዲሁም የወተት የአፍላቶክሲን መጠን መጨመር ለህጻናት መቀጨጭ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

## በሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበር ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርትኢንስቲትዩቱ ድጋፍ መሰጠቱን በተመለከተ፡-

21. ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበር ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርት ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፡፡

22. በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ላይ ድጋፍ የማያደርግላቸው መሆኑን በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ከታዩ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች በኦዲቱ ወቅት ከተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህም በአልሚ ትኩስ ወተት፣ ያቅላ እና ኤሌምቱ ማቀነባበሪያዎች ከውጭ ሃገር በ2007 ዓ.ም የገቡ የማቀነባበሪያ መሣሪያዎች ያላቸው ቢሆንም ከውጭ እስኪገባ ካለው ሂደት በስተቀር ከገባ በኋላ እንዲሁም ከመግባቱ በፊት በኢንስቲትዩቱ በኩል የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩን እንዲሁም በሆላንድ ዴይሪ እና በአደአ የወተት ማቀነባበሪያዎችም በቴክኖሎጂ መረጣ እና በተከላ ላይ የኢንስቲትዩቱ ተሳትፎ አለመኖሩን እና በጅጅጋ ላይፍስቶክ በቅርብ የገቡ የሥጋ ማቀነባበሪያ መሣሪያዎች ከውጭ እስኪገባ ካለው ሂደት በስተቀር ከገባ በኋላም ሆነ ከመግባቱ በፊት በኢንስቲትዩቱ በኩል የተደረገ ድጋፍ አለመኖሩን እና በቴክኖሎጂ መረጣ እና በተከላ ላይ ኢንስቲትዩቱ ተሳትፎ የሌለው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማቀነባበሪያዎቹ ከተደረገላቸው ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. በኦዲቱ ወቅት የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች በሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበር ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና

ሙከራ ምርት ድጋፍ ሊሰጡ ያልቻሉበት ምክንያት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ቴክኖሎጂዎችን ለመመምረጥ፣ ለመገንባት እና ለመትከል አቅም ያላቸው ባለሙያዎች ባለመኖራቸው፣ በሀገራችን የሙከራ ጣቢያዎች ባለመኖራቸው እና የማቀነባበሪያዎቹ የሙያ አቅም ከኢንስቲትዩቱ በላይ በመሆኑ ኢንስቲትዩቱ መደገፍ አለመቻሉን እንዲሁም የኢንስቲትዩቱ መዋቅር ሙሉ በሙሉ ጸድቆ የወጣው ሃምሌ 2006 ዓ.ም ሲሆን የተፈላጊ ችሎታ መስፈርት ኢንስቲትዩቱ በሚፈልገው ደረጃ ከሲቪል ሰርቪስ ጸድቆ የወጣው የካቲት 2007 ዓ.ም በመሆኑ የሰው ኃይል ማሟላት አለመቻሉን ነገር ግን ለወደፊት የኢንስቲትዩቱ አቅም ሲደራጅ እና በቂ ባለሙያዎች ሲኖሩት የሚተገብሩት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

24. በሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበር ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርት ድጋፍ ሊሰጡ ባለመቻላቸው የሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያዎቹ ለቴክኖሎጂ መረጣ፣ ግንባታና ተከላ ከፍተኛ ወጪ እንዲያወጡ በማድረግ ዘርፉ በቀላሉ እንዳይስፋፋ አድርጎታል፡፡

## በሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍ የምርምር ሥራ መከናወኑን እና ቴክኖሎጂዎች ተሰራጭተው መተግበራቸውን በተመለከተ፡-

25. ኢንስቲትዩቱ በሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት፣ ኢንዱስትሪዎቹ የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ በማድረግ እና የውጭ ባለሃብቶች በዘርፉ እንዲሳተፉ በማድረግ ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ኢንዱስትሪዎች ሊያሸጋግር እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ ኢንስቲትዩቱ ከ2005- 2008 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ያሉ ችግሮችን በመለየት ሊለሙ የሚችሉ ወጪ ቆጣቢ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ እና የምርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት ወደ

ኢንዱስትሪዎች አለመሸጋገሩን እንዲሁም ኢንዱስትሪዎቹም የራሳቸውን የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ ሊደግፍ አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች እና ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የማቀነባበሪያዎቹ ባለሞያዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

27. ለማሳያ፡- ስጋን በገፈፉ (carcass) መልክ ከመላክ ይልቅ በተቆራረጠ መልኩ ሊላክ የሚችልበትን የማቀነባበር ሥርዓት አለመዘርጋቱን ፣ ከደጋውና ወይናደጋው የሀገሪቱ ክፍል ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚቀርቡት እንስሳት ሥጋ ቶሎ የመጥቆር ባህሪ ያለው በመሆኑ የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የቆላ ሥጋን ብቻ ለኤክስፖርት መጠቀማቸው ለዘርፉ ከፍተኛ ሥጋት ሆኖ እያለ በምርምር መፍትሄ አለመስጠቱን  እንዲሁም ጠንካራ ሥጋን ማለስለስ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ቢኖሩም ይህን ለመተግበር የሚያስችል ቴክኖሎጂና ሥልት ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከቀረበላቸው አራት የሥጋ ኢንዱስትሪዎች(ሉና፣ ሄልሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ ደ/ዘይት እና ጅጅጋ ላይቭስቶክ ኤክስፖርት ቄራዎች)  እና ወተትና ወተት ውጤቶች ጥራትና ቁጥጥር እንዲሁም ደህንነት ማረጋገጫ ላይ ምርምር ማካሄድ አለመቻሉን ፣ በፍየል ወተት ላይ ጥናት አለመደረጉ እና ወተትን ለረጅም ጊዜ ማቆየት የሚችል ማሽኖችን እንዲጠቀሙ አለማድረጉን (long shelf life machine/UHT/) እንዲሁም በኬሚካል ወተትን የማቆየቱ ሂደት ጠቀሜታውና ጉዳቱ ተለይቶ ለማቀነባበሪያዎቹ ሳይንሳዊ የሆነ ጥናት እንዲሰጣቸው አለመደረጉን በናሙና ተመርጠው ከታዩ ስድስት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) የወተት ማቀነባበሪያዎች በኦዲቱ ወቅት ከቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና በኢንስቲትዩቱ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

28. እንዲሁም በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት የሥጋ (ሉና፣ ሄልሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ ደ/ዘይት እና ጅጅጋ ላይቭስቶክ ኤክስፖርት ቄራዎች) ፣ አምስት የወተት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) እና ሁለት የመኖ (አዲስ አለም ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ታዳሽ የኃይል ምንጮችን የማይጠቀሙ እና

የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ያልተሸፈኑ (Safety tank) የሌላቸው መሆኑን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፣ ይህም ኢንስቲትዩቱ በተለይ ለኢንዱስትሪዎች ከፍተኛ ችግር ሆኖ የሚታየውን የመብራት መቆራረጥ በተወሰነ ደረጃ ማቃለል የሚችለውን ባዮጋዝ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ በናመና ተመርጠው በታዩ ኢንዱስትሪዎች ላይ እንዲገነቡ እገዛ አለማድረጉን እና አልሚ ትኩስ ወተት ማቀነባበሪያ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ እና ውሃን መልሶ አጣርቶ ለመጠቀም የሚያስችል ቴክኖሎጂን ለመጠቀም በዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ የሚያደርግለት እገዛ የሌለ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማቀነባበሪያው ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

29.ስለ ሁኔታው የኢንስቲትዩቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በኢንስቲትዩቱ ያሉ ባለሙያዎች የምርምር ሥርዓት ላይ ግንዛቤ ያላቸው ባለመሆኑ፣ ከምርምር ተቋማት ጋር ቅንጅት በመፍጠር መሥራት ባለመቻሉ እና ምርምርን ለማከናወን የሚያስችል የሰው ኃይልና ቁሳቁሶች ባለመሟላታቸው እና ንዑስ ዘርፉ በቅርብ ጊዜ ወደ ምርምር የመጣ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎቹን የማብቃት እና ከግብርና ምርምርና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር ተቀናጅቶ መሥራት ስለሚጠበቅበት ምክንያቱ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

30.ኢንስቲትዩቱ በሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት፣ ኢንዱስትሪዎቹ የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ አለማድረጋቸው እና የውጭ ባለሃብቶች በዘርፉ እንዲሳተፉ በማድረግ ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ኢንዱስትሪዎች እንዲሸጋገሩ አለማድረጋቸው ዘርፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የተለያዩ ጥራት ያላቸውን የሥጋ፣ ወተትና መኖ ምርቶችን በማምረት ኢንዱስትሪው ተወዳዳሪ እንዳይሆን አድርጓል፡፡ እንዲሁም ኢንዱስትሪዎች ታዳሽ የኃይል ምንጮችን የማይጠቀሙ እና የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ያልተሸፈኑ (Safety tank) የሌላቸው መሆኑ

ኢንዱስትሪዎቹ ወጪ መቆጠብ እንዳይችሉ ከማድረጉም በላይ የአከባቢ ብክለት እንዲኖር ያደርጋል፡፡

## የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ያካተተ ስለመሆኑ፡-

31. የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (Cross Cutting Issues) ያካተቱ ሊሆን ይገባል፡፡

32. የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ዕቅድ ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞችን...) ባካተተ መልኩ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት አፈጻጸሙን ያካተተ ሪፖርት በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ማቅረብ አልተቻለም፡፡ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት የሥርዓተ ጾታ ዘርፍን ለማካተት የሚያስችለው የስርዓተ ጾታ ጉዳይ ባለሙያን በእያንዳንዱ ዕቅድ እንዲሳተፍ የማያደርግ እና የስርዓተ ጾታ ጉዳይን የሚከታተለው በአንድ ባለሙያ (Focal Person) ብቻ በመሆኑ ውጤታማ መሆን አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ለኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

33. ስለ ሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የኢንስቲትዩቱ ስርዓተ ጾታ ባለሙያ ከመ/ቤቱ ሴክተሮች ጋር ተቀናጅቶ ባለመሥራቱ በዚህ ዙሪያ ብዙ አለመሰራቱን እንዲሁም በ2008 ዓ.ም በአነስተኛ መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ ደረጃ ያሉትን በኢንዱስትሪ ሚ/ር መደገፍ ያለባቸው እንደሆነ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በአነስተኛ፣ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የተደራጁትን ወጣቶች፣ ሴቶች፣ አካል ጉዳተኞች በመለየት እንቅስቃሴ የጀመሩ መሆኑን ቢገልጹም የስርዓተ ጾታ ባለሙያን በዕቅድ ወቅት እንዲሳተፍ በማድረግ አብሮ መስራት ስለሚጠበቅባቸው ምክንያቱ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

34.የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (Cross Cutting Issues) ያካተቱ እንዲሆኑ አለመደረጉ ከኢንዱስትሪው ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ እንዳይሆን በማድረግ መንግስት በእስትራቴጂክ ዕቅዱ የያዘውን የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን ተጠቃሚነት ዓላማ ግብ እንዳይደርስ ያደርጋል፡፡

## የኢንስቲትዩቱ ንብረቶች/መሳሪያዎች እና ኬሚካሎች ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን በተመለከተ፡-

35.በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሚመለከቱ ሥራን ለማካሄድ በዕቅድ የተገዙ ንብረቶች/መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸው/የማይሰሩት (Expired/ Damaged) የሆኑት የሚወገዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

36. በኢንስቲትዩቱ 165 ዓይነት ንብረቶች ውሳኔ ያላገኙ እና ጥቅም ላይ የማይውሉ፣ 2 ተሽከርካሪዎች እና 8 የእርሻ መሳሪያዎች ውሳኔ ያገኙ ነገር ግን ያልተወገዱ እንዲሁም 81 ዓይነት ንብረቶች/መሣሪያዎች ያረጁና የተበላሹ መሆኑን እና ዘጠኝ አይነት (ዲያዚኖን፣ ዳይሚትዩት፣ ፍላመብል ሊኪዩድ፣ ላስትራዚን፣ ስተቪን 85 wp፣ አሲቲክ አሲድ 100%፣ ጽሁፍ የሌለው ፈሳሽ፣ ጽሁፍ የሌለው ዱቄት እና ፒኤች ሜትር) የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈና ጥቅም ላይ የማይውሉ ኬሚካሎች እና የላብራቶሪ መሳሪያዎች መኖራቸውን ከማስረጃዎች በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

37. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ከኤሌክትሮኒክስ ጋር የተያያዙትን ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ለማስረከብ ጠይቀው ቦታ የለንም በመባሉ እና ሌሎቹን ለሚመለከታቸው አካላት ለግብርና ሚ/ር፣ ለፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ንብረት ማስወገድ እና ግዥ ኤጀንሲ

ያሳወቁ ቢሆንም እርምጃ አለመወሰዱን እንዲሁም ኬሚካል በሀገር ደረጃ የሚወገድ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

38. በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሚመለከቱ ሥራን ለማካሄድ በዕቅድ የተገዙ ንብረቶች/መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ተይዘው ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉ የመንግስት ንብረት ለብክነት እንዲጋለጥ በማድረግ መሳሪያዎቹ ለታለመላቸው ዓላማ ሳይውሉ እንዲቀሩ ያደርጋል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ሎጅስቲክስ አመራርና ግብይት ዙሪያ ለማቀነባበሪያዎቹ ድጋፍ መስጠቱን በተመለከተ፡-

39. ኢንስቲትዩቱ የዳበረ ልምድ ካላቸው ሀገራት በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም፣ በሥጋ ሎጅስቲክስ አመራርና ግብይት ዙሪያ በእንስሳት ምርቶች ላይ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮችን በማዘጋጀት በገኙ ሀገራት በሚደረጉ መድረኮች ላይ በማስተዋወቅ እና በመዳረሻ ሃገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን እንዲሁም የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦትን በመለየትና እንዲሟሉ በማድረግ ለማቀነባበሪያ ፋብሪካዎቹ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡

40. ኢንስቲትዩቱ በኢንዱስትሪዎቹ ለሚከሰተው የመሣሪያዎች ብልሽትና የመለዋወጫዎች ችግርን አስመልክቶ የሥልጠና እና ድጋፍ አገልግሎት አለመስጠቱን እንዲሁም ከኢንስቲትዩቱ ለሥራ ተልከው ወደ ኢንዱስትሪዎቹ የሚሄዱ ባለሙያዎች በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም ላይ እገዛ ለማድረግ የሚያስችል በቂ የተግባር ክህሎት የሌላቸው መሆኑን እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ውጤቶች በመዳረሻ ሀገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን በመለየት ለኢንዱስትሪዎቹ ያላስተዋወቀ እና ማስረጃውን ያልሰጣቸው/ያላሰራጨ መሆኑን በናሙና ተመርጠው የታዩ አራት (ሄልሚክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ፣ሉና

እና ጅጅጋ ላይፍስቶክ) ኢንዱስትሪዎች በኦዲቱ ወቅት ከተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

41. አሁን ያለው የሥጋ ኤክስፖርት ገበያ በደንበኞች ትዕዛዝ እና ቄራዎች በራሳቸው መንገድ ገበያን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ እንጂ ኢንስቲትዩቱ በሌሎች ሀገራት ያለውን አማራጭ መዳረሻ ገበያዎችን በራሱና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር እና ኢምባሲዎች) ጋር በመሆን ገበያ ማፈላለግ አለመቻሉን እንዲሁም በሥጋ ምርቶች ላይ የሚካሄዱ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮች በጥናት ላይ ያልተመረኮዙ እና ሁሉንም የሥጋ ማቀነባበሪያዎች ያላሳተፉ እንዲሁም ውጤታቸው የማይለካ መሆኑን፣ እንዲሁም በበረዶ የቀዘቀዘ የዳልጋ ከብት ሥጋን መግዛት ወደ ሚፈልጉ ሀገሮች አንጎላ፣ ግብጽ፣ ቻይና፣ ኢራን፣ አልጄሪያና ሞሮኮ ገበያዎች መግባት አለመቻሉን ፣በገዥ ሀገራት በሚደረጉ የምርት ማስተዋወቂያ መድረኮች ላይ የእንስሳት ምርት ላኪዎች ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ የሚጋብዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን እና የሥጋ መዳረሻ ገበያዎችን የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦት ዙሪያ የደሰሳ ጥናቶችን በማከናወን መረጃዎችን በማጠናቀር ቄራዎች እንዲደርሳቸው አለማድረጉን ከማስረጃ እና በናሙና ተመርጠው ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ኢንዱስትሪዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

42. የወተት አቅርቦት ችግር እና በጾም ወቅት የሚፈጠረው የገበያ እጥረት ከፍተኛ በመሆኑ ባለሃብቱ በሥራው እምነት እንዲያጣ እያደረገ መሆኑን እና ሱማሌ እና ጅቡቲ አከባቢ ከፍተኛ የወተት ፍላጎት ያለ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ አከባቢዎቹን ፍላጎት በመለየት ማቀነባበሪያዎቹን ሊደግፍ አለመቻሉን እንዲሁም የወተት ዘርፉ የወጪ ምርቶች የገበያ እስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን የኢንስቲትዩቱ የ2007 ዓ.ም ዕቅድ የሚያመለክት ሲሆን በተለይ በአሁኑ ወቅት ከአፍላቶክሲን ጋር በተያያዘ የማቀነባበሪያዎቹ የገበያ ሁኔታ የተቀዛቀዘ መምጣቱ ለዘርፉ ስጋት ሲሆን በተለይ በአዳማ አከባቢ የሚገኘው ያቅላ ወተት ማቀነባበሪያ ከገበያ

ለመውጣት የተገደደ መሆኑን ለማቀነባበሪያው በኦዲቱ ወቅት ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለመኖ ማቀነባበሪያ ግብዓትነት የሚያገለግሉ የፋብሪካ ተረፈ ምርቶች ለተደጋጋሚ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተጋለጡ በመሆናቸው የዋጋ ጭማሪ እየተስተዋለባቸው መሆኑን እንዲሁም ማቀነባበሪያዎቹ በቂ ገበያ ያለማግኘት እና ለሥራው የሚያስፈልግ የሰው ኃይል ከሚሟላት ይልቅ በተወሰነ ባለሙያዎች ብቻ ሥራን የሚያከናውኑ መሆኑን በወንጂ ሸዋ እና መተሃራ ስኳር ፋብሪካ ዙሪያ የማደለቢያ ጣቢያዎች እና የመኖ ልማት ትስስር የመስክ ሪፖርት 2006 ዓ.ም እና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ሁለት (አለማ ካዎዳይስ እና አዲስ አለም ሞጆ) የመኖ ማቀነባበሪያዎች በኦዲቱ ወቅት በቀረበላቸው መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. እንዲሁም በኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ምርቶች ላይ የሚካሄዱ የንግድ ትርኢቶች እና ባዛሮች በጥናት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ የማያደርግ እና ውጤታቸውንም የማይለካ መሆኑ፤ ይህም የአፍሪካ ላይቭስቶክ ኤግዚቢሽን እና ኮንግረንስ (ከሚያዚያ 30/2006 ዓ.ም እስከ ግንቦት 02/2006 ዓ.ም) በሚሊኒየም አዳራሽ በተካሄደው ላይ የውጪ ገዥዎችን በኤግዚቢሽን እንዲሳተፉ በማስተዋወቅ ደረጃ ውስንነት እንደነበረ፣ Ethio Api Expo በአዲስ አበባና Veterinary Conference በመቀሌ በተመሳሳይ ጊዜ የተካሄደ መሆኑ እና የተጠበቁ ህዝባዊ ድርጅቶችና የክልል ቢሮዎች አለመሳተፋቸው የኤግዚቢሽኑን ውጤታመነት የቀነሱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

44. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም፣ በሥጋ ሎጅስቲክስ አመራር የሙያ ክፍተት መኖሩን፣ ግብይት እና ኤግዚቢሽንን አስመልክቶ ከማቀነባበሪያዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አለመኖሩን፣ የጥራት ችግር በመኖሩ የዋጋ መቀነስ ችግሮች መኖራቸውን እንዲሁም ቴሬሴቢሊቲ በሀገራችን እውን በማድረግ ወደ ዓለም ገበያ በስፋት ለመግባት ስለሚጠቅም

በዚህ ዙሪያ ከእንስሳትና ዓሳ ሃብት ልማት ጋር በጋራ መሰራት ያለበት መሆኑን እና የሥጋ መዳረሻ ገበያዎችን የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦት ዙሪያ የደሰሳ ጥናቶችን በተወሰነ ደረጃ የተደረገ ቢሆንም ከዚህ በበለጠ መስራት ስለሚያስፈልግ አስፈላጊውን የሰው ሃይል በማሟላት ልዩ ትኩረት ተደርጎበት ለወደፊት እንዲሰራ የሚደረግ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም የኢንስቲትዩቱን ባለሙያ የማደራጀት እና በእንስሳት ምርቶች ላይ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮችን በማዘጋጀት በገዥ ሀገራት በሚደረጉ መድረኮች ላይ በማስተዋወቅ እና በመዳረሻ ሃገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን እንዲሁም የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦትን በመለየትና እንዲሟሉ የማድረግ ኃላፊነታቸውን መወጣት ያለባቸው በመሆኑ ምክንያቱ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

45. ኢንስቲትዩቱ የዳበረ ልምድ ካላቸው ሀገራት በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም፣ በሥጋ ሎጅስቲክስ አመራርና ግብይት ዙሪያ በእንስሳት ምርቶች ላይ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮችን በማዘጋጀት በገዥ ሀገራት በሚደረጉ መድረኮች ላይ በማስተዋወቅ እና በመዳረሻ ሃገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን እንዲሁም የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦትን በመለየት እንዲሟሉ አለማድረጉ ማቀነባበሪያዎቹ ውጤታማ እንዳይሆኑ በማድረግ ሀገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት ያለባትን የውጭ ምንዛሬ እንዳታገኝ ያደርጋታል፡፡

## የሥጋ፣ ወተትና መኖ ግብዓት አቅርቦት በዓይነት፣ በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን መደረጉን በተመለከተ፡-

46. ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ የግብዓት አቅርቦት በዓይነት በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱስትሪዎች እንዲለሙ ሊደግፍ፣ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም ዓቀፍ ገበያ በምርቶች እሴት ሰንሰለት በዘርፉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና

ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ምርቶች ፍላጎትና አቅርቦት (Supply Chain) ላይ የደሰሳ ጥናት በማካሄድ ኢንዱስትሪዎቹን ሊደግፍ ይገባል፡፡

47. ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን አቅርቦት እጥረት መንስኤዎችን በመለየት በአቅርቦት ዘርፍ ከተሰማሩ ባለሃብቶችና ተቋማት ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል ደሰሳ ጥናት (Supply chain) በማካሄድ ተግባራዊ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች እና ለማቀነባበሪያዎቹ ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡- የማሽኒያ፣ የኬሚካል፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች...እና የቁም እንስሳት አቅርቦት) በተለይ በሥጋና ወተት ፍላጎትና እንስሳት አቅርቦት ላይ ደሰሳ ጥናት በማከናወን ለማቀነባበሪያዎቹ ያልተሰራጨና ተግባራዊ እንዲደረግ አለመደረጉን፣ በተጨማሪም የእንስሳት አቅርቦትን ችግር ለመፍታት የግል ባለሃብቶችና የቁራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡ እና እንዲያደልቡ ብሎም ከይዞታቸው ለእርድ እንዲያቀርቡ የእንስሳት እርባታ (ራንች) እንዲያቋቁሙ አለመደረጉን እና ኤክስፖርት ቄራዎች እንስሳት የሚያቀርቡ ማህበራትና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችና ነጋዴዎችን በመለየት ከቄራዎች ጋር ማስተሳሰር አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎቹ በተደረገ ቃለ መጠይቅ እና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

48. እንዲሁም ጅጅጋ ፊቅ አከባቢ ከፍተኛ የፍየል አቅርቦት ያለ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ለክልሉ ትኩረት በመስጠት በአከባቢው የሚገኙትን አቅራቢዎች ከኢንዱስትሪዎቹ ጋር የማስተሳሰር ሥራዎችን ያላከናወነ መሆኑን በጅጅጋ ክልል ለኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ከቀረበላቸው መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

49. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ማቀነባበሪያዎቹ ከኢንስቲትዩቱ በላይ አቅራቢዎችን የሚያውቁ መሆኑን፣ የእንስሳት እርባታን አስመልክቶ የመሬት ችግር መኖሩን እና ከክልሎች ጋር ተቀናጅቶ መስራት አለመቻሉን እንዲሁም የሰው ኃይል እጥረት መኖሩንና የፓኬጂንግ ዳይሬክቶሬት ባለመቋቋሙ የተፈጠረ ቢሆንም ወደ ፊት ችግሩን ለመፍታት የሚሰሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

50. ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ የግብዓት አቅርቦት በዓይነት በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱሰትሪዎች እንዲለሙ ሊደግፍ አለመቻሉ እንዲሁም በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ምርቶች ፍላጎትና አቅርቦት (Supply Chain) ላይ የደሰሳ ጥናት አለመካሄዱ ማቀነባበሪያዎቹ የግብዓት እና የእንስሳት አቅርቦት በሰፊው እንዳያገኙ በማድረግ ማቀነባበሪያዎቹ በሙሉ አቅማቸው ማምረት እንዳይችሉ አድርጓል፡፡

## <u>ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት መስራቱን በተመለከተ፡-</u>

51. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት(በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ግብርና ሚ/ር፣ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ክልሎች፣ አየር መንገድ፣ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ትራንስፖርት ሚ/ር) ጋር በመቀናጀት መስራት ይኖርበታል፡፡

52. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት(በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ግብርና ሚ/ር፣ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ክልሎች፣ አየር መንገድ፣

ኤርፖርቶች ድርጅት እና ትራንስፖርት ሚ/ር) ጋር በመቀናጀት ውጤታማ የግብይት ሥርዓትን በመዘርጋት አዳዲስ የገበያ መዳረሻዎችን በመለየትና በማስተዋወቅ ኢንዱስትሪዎቹ አቅማቸውን ሊያሳድግ አለመቻሉን፣በዘርፉ የአገር ውስጥ ምርምር አቅም እንዲጠናከር እና የዘርፉን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎት እንዲሟላ ሊያደርግ እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራሮችን በመዘርጋት የመግባቢያ ሰነድ (MOU) በመፈራረም ተግባራዊ ማደረግ አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎችና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

53. ኢንስቲትዩቱ የትምህርት፣ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር ፎረም ከ2 ዓመት በፊት ያቋቋመ ቢሆንም በቀጣይነት ለመተግበር የሚያስችለው መመሪያ ወይም ማንዋል አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ሊገባ አለመቻሉን፤ ይህም በዘርፉ የአገር ውስጥ ምርምር አቅም እንዲጠናከር እና የዘርፉን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎትን ለማሟላት በኢንዱሰትሪዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በጋራ የተከናወኑ ተግባራት አለመኖሩን እና ኢንስቲትዩቱ በወጪ ንግድ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር፣ ከባንኮች፣ ከጉምሩክ፣ ከአየር መንገድ፣ ከግብርና ሚ/ር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት እና ለመከታተል እንዲሁም ችግር ሲገጥም መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል መድረክ/ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን ፣ ኢንስቲትዩቱ የኮልድ ቼይን ሰንሰለት ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ከቄራዎች፣ ከአየር መንገድ፣ ከኤርፖርቶች ድርጅትና ከትራንስፖርት ሚ/ር ጋር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በመዘርጋት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሞ በሰነዱ መሰረት ወደ ተግባር ሊገባ አለመቻሉን በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች ከቀረቡ መጠይቆች ለመረዳት መቻሉ፣ እንዲሁም የትስስር ፎረሙ ለማቀነባበሪያዎቹ ያለው ጠቀሜታ አነስተኛ መሆኑን እና የወደፊት ጠቀሜታውን ባለመረዳታቸው ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስቸግራቸው መሆኑን በናሙና ተመርጠው የታዩት

ስድስቱ (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ኤሊምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት)፣ አራቱ የሥጋ ፋብሪካዎች (ሄልሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ፣ ሉና እና ጅጅጋ ላይቭስቶክ) እና ሁለቱ የመኖ (አዲስ አለም ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) ማቀነባበሪያዎች መግለጻቸው፤

54. ኢንስቲትዩቱ በተለይም በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር ውጤታማ የምርት የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖራቸው በማድረግ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ማድረስ አለመቻሉን፣ የህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው አቅማቸውን በማሳደግ የእርድ እንስሳት እና ወተት እንዲያቀርቡ በየደረጃው ካለው ህብረት ሥራ ማህበራት አደራጅ መ/ቤቶች ጋር በጋራ አለመሥራቱን፣ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የሚሰጠውን ድጋፍ ተደራሽ ለማድረግ በክልሎች የራሱ መዋቅር በተዋረድ የሌለው ቢሆንም በኢንዱስትሪዎቹ አከባቢ ከሚገኙ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው በከተማ መስተዳድር የንግድና ኢንዱስትሪ የሥራ ሂደቶች፣ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች እና ከእንስሳት ሃብት ልማት ኤጀንሲዎች ጋር በቅንጅት አለመስራቱን በኦዲቱ ወቅት ለሉሜ፣ ጅጅጋ እና ሃዋሳ ከተማዎች ለሚገኙ የመ/ቤቶቹ የበላይ ኃላፊዎች ከቀረበ መጠይቅ እና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

55. ኢንስቲትዩቱ በወተት ዘርፍ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የግል ተቋማት መካከል ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ አለማድረጉን፤ ይህም የወተት ማቀነባበሪያዎች ማህበር ከዚህ በፊት በ2003 እና በ2005 ዓ.ም ተቋቁሞ የፈረሰ ሲሆን በ2006 ዓ.ም እንደገና የተቋቋመ ቢሆንም ማህበሩ በተጠናከረ ሁኔታ ወደ ተግባር መግባት አለመቻሉን በናሙና ተመርጠው የታዩ ስድስቱ (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ኤሊምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) ማቀነባበሪያዎች የገለጹ ሲሆን በሀገሪቱ ወደ 34 የሚሆኑ የወተት ማቀነባበሪያዎች ቢኖሩም እስከ 21/04/2008 ዓ.ም ድረስ የማህበሩ አባል መሆን የቻሉት 16 ማቀነባበሪያዎች ብቻ መሆናቸውን ማቀነባበሪያዎቹ ገልጸዋል፤ በመሆኑም ኢንስቲትዩት ማህበሩን

በማጠናከር እና ሁሉንም ማቀነባበሪያዎች ተሳታፊ በማድረግ ማህበሩ ወደ ተግባር እንዲገባ ሊያደርግ አለመቻሉን በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ከታዩት ስድስቱ ማቀነባበሪያዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

56. ስለ ጉዳዩ የኢንስቲትዩቱ  የበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የትስስር ፎረሙ ዩኒቨርሲቲው በበላይነት ተቀብሎ መሥራት ባለመቻሉ እና ስብሰቡ በራሱ መጀመሪያ ችግር ያለበትና አቅጣጫ ለይቶ መሄድ በለመቻሉ፣ የወተት ማህበርን በተመለከተ በፊት ተደራጅቶ የነበረው በፕሮዳክሽን ላይ በመሆኑ አሁን በአዲስ መልክ ወደ ፕሮሰሲንግ አደረጃጀት እንዲመጡ በማድረግ ላይ መሆናቸውን እና ከኢንዱስትሪዎቹ እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የጠበቀ ግንኙነት መፍጠር ባለመቻሉ ሲሆን ለወደፊት ተጠናክሮ አብሮ መሥራት የሚጠበቅባቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

57. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶ አለመሥራቱ ኢንዱስትሪዎቹ ጥራት ያለው አቅርቦት እንዳያገኙ፣ ጥራት ያለውን ምርት በማምረት በአለም አቀፍ ገበያ ተሳታፊ መሆን እንዳይችሉ እና ከተለያዩ አካላት በምርምር የሚገኙ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንዳይሆኑ አድርጓል፡፡

## <u>በሥጋና ወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ተወዳዳሪ በመሆን ለአገር ውስጥና ለውጭ ሀገር በበቂ ሁኔታ ምርቶችን የሚያቀርቡ ስለመሆኑ፡-</u>

58. ኢንስቲትዩቱ በሥጋና ወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት የሚያስችል (import substitution) ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ መቅረብ እንዲችሉ በማድረግ ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶች በአገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

59. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች እና በናሙና ተመርጠው በመስክ ሥራ በታዩ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶችን በሃገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ የሚያስችል ስልት ኢንስቲትዩቱ ቀይሶ ተግባራዊ አለማድረጉን ለማወቅ ተችሏል፤ ይህም በወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት በሚያስችል (Import substitution) ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ እንዲችሉ አለመደረጉ እና ከ2005- 2007 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የወተትና ወተት ውጤቶች ኤክስፖርት ዕቅድ አለመያዙ ለዘርፉ ትኩረት አለመሰጠቱን የሚያመለክት ሲሆን የ2006 ዓ.ም የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ድርጅትታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል ዕቅድ ማስረጃ እንደሚያመለክተው በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ 44,604,941.56 ዶላር የሚያወጣ 17 ዓይነት ምርት ወደ ሃገር ውስጥ መግባቱን እና ይህም ወጪ በዓመት ሲሰላ 8,920,988.31 ዶላር እንደሚሆን እንዲሁም ወደ ሃገሪቱ የሚገባው የወተትና ወተት ውጤቶች አማካይ ዕድገቱ 35.95% እንደሆነ ያሳያል፤ በተጨማሪም አሁን በ2007 ዓ.ም የገቢያ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በ20 ሚሊዮን ዶላር በዓመት ወተት ከውጭ ሃገር ወደ ሀገራችን የሚገባ መሆኑን የሚያስረዳ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ይህን ወጪ ለመቀነስ የሚያስችል ድጋፍ ለማቀነባበሪያዎቹ መስጠት አልቻለም፡፡

60. የሀገራችን የሥጋ ማቀነባበሪያዎች በተወሰኑ አይነት (በፍየል እና በግ) ሥጋ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በሌሎች የተቀነባበረ የፍየል፣ በግ፣ ዳልጋ ከብት እና ግመል ወ.ዘ.ተ ሥጋ፣ የሀገራችን የወተት ማቀነባበሪያዎች ደግሞ ፓስቸራይዝድ ወተት፣ እርጎ፣ አይብ፣ የገበታ ቅቤ እና የምግብ ቅቤ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በሌሎች ክሬም፣ የተፈጨ ቺዝ፣ ፕሮቫለን ቺዝ፣ ሞዞሬላ ቺዝ፣ ፌታ ቺዝ፣ እስሞክድ ቺዝ፣ ፎንቲና ቺዝ ወ.ዘ.ተ ላይ ትኩረት አድርገው የማይሠሩ መሆኑን እንዲሁም በሙሉ አቅማቸው እንዳይሰሩ ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳት

ኤክስፖርት ቄራዎች በሚፈልጉት ዓይነት፣ ዕድሜ፣ ክብደትና ዋጋ እንዲቀርብ ክትትል አለመደረጉን እና ብዛትን አስመልክቶ የሥጋ እና ወተት ማቀነባበሪያዎቹ የማምረት አቅም ያላቸው ቢሆንም በሙሉ አቅማቸው እያመረቱ አለመሆኑን በናሙና ተመርጠው ከታዩ ኢንዱስትሪዎችዎች እና በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ለማሳያ፡-

| ተ.ቁ | የማቀነባበሪያው ሥም | በዓመት የማምረት አቅም በቶን | በ2007 ዓ.ም ያመረተው በቶን | እያመረተ ያለው ከማምረት አቅሙ ጋር ሲነጻጸር በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሉና ኤክስፖርት ቄራ | 5,230 | - | - |
| 2 | ሂልሜክስ/ሃሽም | 10,400 | 5,000 | 50% |
| 3 | ኤልፎራ ደ/ዘይት | 4,608 | 2,304 | 43% |
| 4 | አክሽከር | 12,000 | 4,800 | 40% |
| ተ.ቁ | የማቀነባበሪያው ሥም | የማምረት አቅም በቀን | አሁን በ2008 ዓ.ም እያመረተ ያለው በቀን | እያመረተ ያለው ከማምረት አቅሙ ጋር ሲነጻጸር በፐርሰንት |
| 1 | አልሚ ትኩስ ወተት | 20,000 ሊትር | ከ400-2,500 ሊትር | 2% - 12.5% |
| 2 | ሆላንድ ዴይሪ | 20,000 ሊትር | 12,000 ሊትር | 60% |
| 3 | አደአ ወተት የህብረት ሥራ ማህበር | 15,000 ሊትር | 6,500 ሊትር | 43% |
| 4 | ጀነሲስ ፋርም | 6000 ሊትር | 4000 ሊትር | 66.6% |

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ሁሉም ማቀነባበሪያዎች ማምረት ከሚችሉት በታች እያመረቱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች እና ከኢንስቲትዩቱ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

61. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፤ የምርት ጥራትና የውጭ ሃገር ገበያ የማግኘት ችግር በመኖሩ፣ ማቀነባበሪያዎቹ የራሳቸው ፋርም የሌላቸው በመሆኑ ፣ የእንስሳት ዝርያ ችግር በመኖሩ እና ከሀገር በቀል ላሞች የሚገኘው ወተት ምርት አነስተኛ በመሆኑ እንዲሁም ካምፓኒዎች ራቅ ካለ ቦታ ወተትን ማሰባሰብ የትራንስፖርት ዋጋ ከፍ ያደርጋል ብለው ስለሚሰጉ ርቀው ወተትን ከማሰባሰብ ይልቅ አቅራቢያቸው ባለው ወተት ላይ ብቻ የሚረባረቡ በመሆኑ የተፈጠረ ቢሆንም በጂቲፒ 2 በዕቅድ ተይዞ ወደ ሥራ ሊገባ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

62. ኢንስቲትዩቱ በሥጋና ወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት በሚያስችል መልኩ ድጋፍ አለመስጠቱ ሥጋና ወተት ለጤንነት ጠቃሚ በመሆኑ ጤናማ ዜጋ እንዳይፈጠር አስተዋጽኦ ከማደረጉም በላይ ሀገሪቷ ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ያላት ቢሆንም ከዘርፉ ባለመጠቀሟ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እንድታወጣ አድርጓታል፡፡

## ኢንስቲትዩቱ ሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ማድረጉን በተመለከተ፡-

63. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ሊያዘጋጅና ሊያሰራጭ፣ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች ጠቋሚ ጥናት ሊያደርግ፣ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሰጥ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሊያካሂድ እና በዘርፉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲወገዱ ድጋፍ በመስጠት አዳዲስ ባለሃብቶች በዘርፉ በብዛት እንዲሰማሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡

64. በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎች ያልተዘጋጁና ያልተሰራጩ፤ እንዲሁም ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች ጠቋሚ ጥናት በማድረግ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማደረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ

ችግሮች መፍትሄ ሊሰጥ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ ያነጋገራቸው የሉሜ፣ ጅጅጋ እና ሃዋሳ አከባቢ የበላይ ኃላፊዎች የገለጹ ሲሆን በአፈጻጸም ወቅት ለተከሰቱ ችግሮች ስለተሰጠው የማስተካከያ እርምጃ የሚያመለክት ማስረጃ በናሙና ከታዩት ማቀነባበሪያዎች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቆ ማግኘት አልተቻለም፤ እንዲሁም ሁሉንም ክልሎች በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ተሳታፊ ማድረግ አለመቻሉ፤ ይህም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ ሶማሌ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና የትግራይ ክልሎች በዘርፉ ትኩረት ያልተሰጣቸው መሆኑን ለእንስሳት ሀብት ልማት ኢንቨስትመንት የሚውሉ መሬቶች ለመለየት በክልሎች ከተደረገ ጥናት የመስክ መልስ ሪፖርት 2004 ዓ.ም ለመረዳት ተችሏል፡፡

65. እንዲሁም ኢንቨስትመንቱ እንዳይስፋፋ እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮች በአፋጣኝ መፍትሄ የማይሰጣቸው መሆኑ፤ ለምሳሌ፡- በናሙና ተመርጠው የታዩት አራቱ የሥጋ፣ ስድስቱ የወተት እና ሁለቱ የመኖ ማቀነባበሪያዎች እንደገለጹት የመብራት መቆራረጥ በቀን ከብር 10,000 እስከ 15,000 የነዳጅ ወጪ እንደሚያስወጣቸው እና ለመሳሪያዎች ብልሽት እየዳረጋቸው መሆኑን እንዲሁም ከማስፋፋት ጋር በተያያዘ የራሳቸው እንስሳት ማቆያና ማደለቢያ እንዲኖራቸው የሚጠይቁትን መሬት የማያገኙ መሆኑን እና በልማት ባንክ በኩል ለዘርፉ ትኩረት ባለመስጠት የሚሰጣቸው ብድር የሚጓተትበት ሁኔታ መኖሩን መግለጻቸው፤ አልሚ ትኩስ ወተት የራሱ የሆኑ 27 የወተት ላሞች ያሉት ቢሆንም ከማቀነባበሪያው ቦታ ከ100 ኪ.ሜ በላይ ርቀት ባለው ቦታና በመኖሪያ አከባቢ የሚያረቡበት ሁኔታ መኖሩን እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ብዙ ጊዜ በመድረክ ሰብስቦ በመወያየት መረጃን በማሰባሰብ ከመርካት ይልቅ የኢንስቲትዩቱ ባለሞያዎች ማቀነባበሪው ድረስ በመሄድ አብሮ መስራት አለመቻላቸውን በናሙና የታዩ ስድስቱም (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ኤሊምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) ማቀነባበሪያዎች ከተደረጋላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

66. አደአ የወተት ህብረት ሥራ ማህበር የተመጣጠነ የእንስሳት መኖን በቀን በሶስት ጊዜ ፈረቃ ከ750 ኪ.ግ በላይ ማቀነባበር የሚያስችለው መሳሪያ ያለው ቢሆንም እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት አለመስጠቱን በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የመስክ ምልከታ ለማወቅ ተችሏል፤ ኢንስቲትዩቱ ይህን ዘርፍ ከማስፋፋት እና ውጤታማ ከማድረግ አኳያ የማቀነባበሪያውን ችግር በመለየት ማቀነባበሪያው ወደ ሥራ እንዲገባ ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለመቻሉን በኦዲቱ ወቅት ለአደአ ወተት ማቀነባበሪያ የበላይ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

67. የኢንስቲትዩቱ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ባለመኖሩ እና በተለይ ከብድር ጋር በተያያዘ የውጭ ምንዛሬ እጥረት በመኖሩ እንዲሁም ባለሃብቶቹ በብድር ለሥጋ እና ወተት ዘርፍ የሚወስዱትን ገንዘብ በትክክል ለዘርፉ የማያውሉበት ሁኔታዎች በመኖሩ ሊፈጠር መቻሉን የገለጹ ሲሆን ከመኖ ጋር ተያይዞ የተነሳው ማቀነባበሪያዎቹ ጥያቄ ባለማቅረባቸው እና ችግሩ መኖሩን ባለማወቃቸው የተከሰተ መሆኑን ቢገልጹም ኢንስቲትዩቱ ክትትል በማድረግ ማነቆዎችን መፍታት ስለሚጠበቅበት ምክንያቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

68. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ለማድረግ የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን አለማዘጋጀቱ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን አለማካሄዱ እና ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች ጠቃሚ ጥናት በማደረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ አለመስጠቱ ዘርፉ እንዳይስፋፋ እና ውጤታማ እንዳይሆን እንዲሁም በዘርፉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ወደ ኢንዱስትሪዎቹ እንዳይሸጋገር አድርጓታል፡፡

## <u>በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ዙሪያ ያሉ መልካም ተሞክሮዎች ተቀናብረው ተግባራዊ የተደረጉ ስለመሆኑ፡-</u>

69. በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎች ተለይተው ተሞክሮዎቹ ተቀናብረው በኤክስፖርት

ቁራዎች፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ተግባራዊ (implement) ሊደረጉ ይገባል፡፡

70. ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎችን ለይቶ ተሞክሮዎቹን አቀናብሮ ለማቀነባበሪያዎቹ የማያሰራጭና ተግባራዊነቱን የማይከታተል መሆኑን በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ይህም፡- በኢንስቲትዩቱ የተቀናበሩና የተሰራጩ መልካም ተሞክሮ ሰነዶች ኢንዱስትሪዎቹ ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸው እና የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎችም ወደ ውጪ ሃገር ሄደው ከመጡ በኋላ ለማቀነባበሪያዎቹ ስላዩዋቸው ተሞክሮዎች ያገኙትን ልምድ የማያካፍሉዋቸው መሆኑን በናሙና ተመርጠው የታዩት ሶስት የሥጋ (ሄልሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ እና ሉና) ፣ ስድስት የወተት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) እና ሁለት የመኖ (አዲስ አለም ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎቹ በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

71. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ኢንስቲትዩቱ በሰው ኃይል አለመደራጀቱን እና የአቅም ውስንነት መኖሩን የገለጹ ቢሆንም ለኢንስቲትዩቱ የተፈቀደው የሰው ኃይል እንዲሟላ በማድረግ የአቅም ግንባታ ሥራ ማከናወን ከኢንስቲትዩቱ የሚጠበቅ በመሆኑ ምክንያቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

72. በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎች ተለይተው ተሞክሮዎቹ ተቀናብረው በኤክስፖርት ቄራዎች፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ተግባራዊ (implement) አለመደረጉ ኢንዱስትሪዎቹ አዳዲስ ቴክኖሎጂን እንዳይጠቀሙ በማድረግ ከዓለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪነት ውጪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

**ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች የተደራጁና ለሚመለከተው አካል የተሰራጩ መሆኑን በተመለከተ፡-**

73. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎችን ዝርዝር፣ የክልሎችን የእንስሳት አቅርቦት መጠን፣ የወተት ሃብትና የመኖ ማምረት አቅምና ሌሎች መረጃዎች በማሰበሰብ፣ በመተንተን እና በዳታ ቤዝ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች በቀላሉ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

74. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያና ሌሎች መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች ሊያሰራጭ አልቻለም፤ ይህም፡- ኢንስቲትዩቱ የውጭ ገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ በመተንተን እና አደራጅቶ በመያዝ ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት እና የወጪ ምርቶች የገበያ እስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን የኢንስቲትዩቱ የ2007 ዓ.ም ዕቅድ ያመለክታል፤ እንዲሁም እስከ አሁን በኢንስቲትዩቱ የተሰራጩ መረጃዎች በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች እንዲሁም በአከባቢው የሚገኙ የከተማ ኢንዱስትሪ የሥራ ሂደቶች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ማቅረብ አልቻሉም፡፡

75. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የሚውሉ የኢንቨስትመንት ቦታዎችን በዝርዝር ለይቶ እንዲታወቁ በማድረግ መረጃውን በዳታ ቤዝ በማጠናቀር ለባለሃብቶች በቀላሉ መስጠት አለመቻሉን ፣ ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ የሚገኙትን የክልሎች የወተት ሃብት(Milk Shed)ና የመኖ የማምረት አቅም እንዲሁም የእንስሳት አቅርቦት መጠን በመለየት መረጃዎችን ማደራጀት አለመቻሉን እና የእንስሳት ዱካን (Tracibility) ለመመዝገብ የሚያስችል መዝገብ (records) እንዲዘጋጅና ተግባራዊ እንዲደረግ በማድረግ የእንስሳት ጤና ሥርዓትና ቁጥጥርን አስመልክቶ

መረጃዎችን ለተቀባይ ሀገራት የማድረስና የማስተዋወቅ ሥራ አለማከናወኑን በናሙና ተመርጠው ከቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው የሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች እና ከኢንስቲትዩቱ ተሰብስበው ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

76. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ስለ ጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ዘርፉ በሰው ኃይል ባለመጠናከሩ እና የገበያ እና መረጃ አያያዝ ክፍል የተጠናከረ ባለመሆኑ የተፈጠረ ችግር መሆኑን እንዲሁም ለወደፊት ዘርፉን ማጠናከር እንደሚጠበቅባቸው ገልጸዋል፡፡

77. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎችን ዝርዝር፣ የክልሎችን የእንስሳት አቅርቦት መጠን፣ የወተት ሃብትና የመኖ ማምረት አቅምና ሌሎች መረጃዎች በማሰበሰብ ለተጠቃሚው እንዲሰራጭ አለማድረጉ ዘርፉ እንዳይስፋፋ አስተዋጽኦ በማድረግ ሀገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የውጭ ምንዛሬ እንዳታገኝ ያደርጋል፡፡

**<u>ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት መዳረሻ ገበያ እስኪደርስ ድረስ ክትትል እና ቁጥጥር በማድረግ ለቄራዎች ግብረ መልስ በመስጠት አፈጻጸሙን ያሳደገ መሆኑን በተመለከተ፡-</u>**

78. ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት ወደ ሚላኩባቸው መዳረሻ ገበያዎች እስኪደርሱ ድረስ ሱፐርቪዥን ሥራ በማድረግ ለቄራዎች እና ለወተት ማቀነባበሪያዎች ግብረ- መልስ በመስጠት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበሩ በማድረግ የማቀነባበሪያዎቹን አፈጻጸም ሊያሳድግ ይገባል፡፡

79. ጥራቱን ጠብቆ የሄደውን ኮልድ ቼይን ሥርዓት ኤርፖርት አከባቢ ላይ የሚቋረጥበት ሁኔታ መኖሩ፤ ይህም ሥጋ ማውረድ ላይ የሚሰሩ ሰራተኞች ስለ ሥጋ አያያዝና አጠባበቅ በቂ ዕውቀት ስለሌላቸው መኪኖችን ክፍት ትተው በመሄድ ሥጋውን ለሙቀት እንዲጋለጥ የሚያደርጉበት እና ሥጋውን

በሚሸከሙበት ወቅት በአግባቡ የማይዙ እንዲሁም ሥልጠና የተሰጣቸው ቢሆንም በተግባር ክትትል ስለማይደረግባቸው ችግሩ አሁንም እተስተዋለ መሆኑን በናሙና ተመርጠው በኦዲቱ ከታዩ ሶስት (ሃሽም/ሂልሜክስ፣ ኤልፎራ እና ሉና ቄራዎች) በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

| ተ.ቁ | የኢንዱስትሪው ስም | የአፈጻጸም መጠን በቶን | | ልዩነት በቶን | ገቢ በሚሊዮን ዶላር | | ልዩነት በሚሊዮን ዶላር | አፈጻጸም በሚሊ.የ አሜ. ዶላር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | | 2005 ዓ.ም | 2006 ዓ.ም | | የ2007 ዓ.ም |
| 1. | ሉና ኤክስፖርት ቄራ | 4,285.90 | 3,299.158 | (986.74) | 20.75 | 17.978 | (2.772) | 25.99 |
| 2. | ሂልሜክስ/ሃሽም ኤክስፖርት ቄራ | 1,586 | 1,203.036 | (382.96) | 7.67 | 5.769 | (1.901) | 7.67 |
| 3. | ኤልፎራ ደ/ዘይት ኤክስፖርት ቄራ | 1,975.80 | 1,683.117 | (292.68) | 11.03 | 9.540 | (1.49) | 6.18 |
| 4. | አክሽከር ኤክስፖርት ቄራ | - | 815.303 | 815.303 | - | 2.306 | 2.306 | 1.42 |
| | **ድምር** | **7,847.7** | **7,000.614** | **(847.077)** | **39.45** | **35.593** | **(3.857)** | **41.26** |

80. የሥጋ ኢንዱስትሪዎች የዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟሉ ምርቶች ለሃገር ውስጥና ለዓለም ገበያ በስፋት ማቅረብ አለመቻላቸውን ለማወቅ መቻሉ፤ይህም በናሙና ተመርጠው የታዩ የሥጋ ኢንዱስትሪዎች (ሉና፣ ሂልሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ ደ/ዘይት እና አክሽከር ኤክስፖርት ቄራዎች) አፈጻጸም ከ2005 ዓ.ም የ2006 ዓ.ም እየቀነሰ የሚሄድበት ሁኔታ መስተዋሉ ለዘርፉ ስጋት መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የ2005 ዓ.ም እና 2006 ዓ.ም የአፈጻጸም ሪፖርቶች ለመረዳት ተችሏል፡፡

ለማሳያ፡-

ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው ሉና፣ ሂልሜክስ/ሃሽም እና አክሽከር ቄራዎች ከ2005 ዓመት የ2006 ዓ.ም አፈጻጸም እየቀነሰ መሄዱን ከማስረጃ ለመረዳት

ተችሏል፡፡ነገር ግን የ2007 ዓ.ም አፈጻጸም በአጠቃላይ 5.667 በሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ጭማሪ ማሳየቱን ለመረዳት ተችሏል፡፡

81. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የቁጥጥር ሥራውን ለመስራት ያልተቻለበት በኢንስቲትዩቱ የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ እና በመስክ ሄዶ ለመከታተል እና ግብረ መልስ ለመስጠት ያልተቻለው የመንግስት ውሎ አበል በቂ ባለመሆኑ ምክንያት መሆኑን የገለጹ ሲሆን አፈጻጸሙን አስመልክቶ በዘርፉ የእንስሳት ጤና አጠባበቅ እና የሪዚዱዋል ላብራቶሪ በአገራችን ባለመኖሩ መሆኑን እና ወደ ፊት ትኩረት ተደርጎ ከባለድርሻ አካላት ጋር መሰራት እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

82. ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት ወደ ሚላኩባቸው መዳረሻ ገበያዎች እሰኪደርሱ ድረስ ሱፐርቪዥን ሥራ በማድረግ ለቄራዎች እና ለወተት ማቀነባበሪያዎች ግብረ- መልስ በመስጠት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበሩ በማድረግ የማቀነባበሪያዎቹን አፈጻጸም ሊያሳድግ አለመቻሉ ዘርፉ እንዲዳከም በማድረግ ኢንዱስትሪዎቹ ከገበያ እንዲወጡ ያደርጋል፡፡

## <u>ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር ላይ ተሳትፈው ውጤት ያላስመዘገቡ ኢንዱስትሪዎችን በመለየት የኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ማድረጉን በተመለከተ፡-</u>

83. ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታ ያልጀመሩ፣ ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት የኢንቨስትመንት ውሳኔዎች እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፡፡

84. ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት ኢንቨስትመንት ውሳኔ እንዲያገኙ ሊያደረግ አለመቻሉ፤ ለማሳያ ያህል፡- አሽራፍ ኤክስፖርት ቄራ በባህርዳር ከተማ በ5.5 ሄ/ር ላይ አሽራፍ በተባለ ሱዳናዊ ባለ ሃብት ከ9 ዓመት በፊት ግንባታው ተጀምሮ በ2002 ዓ.ም የተመረቀ ሲሆን ቄራው እጅግ ዘመናዊና በቀን 2700 በግና ፍየል እንዲሁም 540 የዳልጋ ከብት የማረድ አቅም ያለው ቢሆንም ቄራው በ2004 ዓ.ም በበረዶ የቀዘቀዘ የዳልጋ ከብት ሥጋ መላክ ጀምሮ ያቋረጠ እና ከገበያ ውጪ መሆኑን እንዲሁም አበርገሌ ኤክስፖርት ቄራ በመቀሌ ከተማ በ3 ሄ/ር መሬት ላይ በትግራይ መልሶ ማቋቋም ድርጅት ተገንብቶ በ2002 ዓ.ም ሥራ የጀመረ ዘመናዊ ቄራ ሲሆን ቄራው 950 በግና ፍየል እንዲሁም 240 ዳልጋ ከብት በቀን የማረድ አቅም ያለው እና የቀዘቀዘ የዳልጋ ከብት ሥጋ ኤክስፖርት ሲያደርግ ቆይቶ ከዓመት በፊት ከገበያ ውጪ የሆነ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

85. የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የእንስሳት አቅርቦት ችግር በመኖሩ፣ ወደ አዲስ አበባ ለማምጣት ተጨማሪ ወጪ የሚያወጡ በመሆኑ እና እርምጃ የመውሰዱ ሥራ በዋናነት የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኃላፊነት ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ለባለሃብቶች ወደ ንዑስ ዘርፉ እንዲገቡ ከሚሰጠው ድጋፍ ባልተናነሰ በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታቸውን የሚያዘገዩትንም ሆነ ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለሚመለከተው አካል ሲያሰውቅ የቆየ መሆኑን የገለጹ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ማቀነባበሪያዎቹ ሲቋቋሙ ጀምሮ በጥናት እንዲቋቋሙ በማደረግ አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ የሚጠበቅበት በመሆኑ ምላሹ ተቀባይነት የለውም፡፡

86. ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታ ያልጀመሩ፣ ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት የኢንቨስትመንት ውሳኔዎች እንዲያገኙ አለመደረጉ ለዘርፉ ተብሎ የተሰጠውን የኢንቨስትመንት ቦታ ላልተፈለገ ወይም ከዓላማ ውጪ ለሆነ ተግባራት እንዲያውሉት ያደርጋል፤ ይህ ደግሞ ለዘርፉ መዳከም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

## <u>በኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ወተትና መኖ ዙሪያ የሚሰጡ ሥልጠናዎች ውጤታማነትን በተመለከተ፡-</u>

87. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ከሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ውጤታቸውም መለካት የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

88. በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በደሰሳ ጥናት (need assessment) ላይ የተሞረኮዙ እና ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ተግባር ተኮር ሥልጠና አለመሆኑን ከሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች የበላይ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፤ ይህም ሥልጠናው የሥጋ እና የወተት ገበያ በቀዘቀዘ ወቅት (ለወተት ማቀነባበሪያዎች በጾም ወቅት እና ለሥጋ ማቀነባበሪያዎች ሥጋ ወደ አረብ ሀገራት የሚላክ በመሆኑ ከአረፋ እና ከሌሎች የሙስሊም በዓላት ወቅት ውጪ) ላይ ብቻ የማይሰጥ በመሆኑ ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸውን ባለሙያ ለመላክ የሚገደዱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማቀነባበሪያዎቹ በቀረቡ ቼክ ሊስቶች እና ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

89. ስለሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የባለሙያ እጥረት  እና የቁሳቁስ ችግር በመኖሩ ሥልጠናውን ተግባር ተኮር

ማድረግ አለመቻሉን እና በፍላጎት ላይ የተመረኮዘ ለማድረግ የውሎ አበል በቂ አለመሆኑን የገለጹ ቢሆንም ባለሙያ በማሟላት ዓላማቸውን ለማሳካት መስራት ስለሚጠበቅባቸው የሰጡትን ምክንያት ለመቀበል ያዳግታል፡፡

90. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ከሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ውጤታቸውም መለካት የሚችሉ አለመሆናቸው የሥልጠናው ዓላማ እንዳይሳካ ከማድረጉም በላይ ለሥልጠና የወጣው ወጪ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

## <u>በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን በመስክ በመከታተል የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቡን በተመለከተ፡-</u>

91. በነባር፣ ሥራ በጀመሩ እና በግንባታ ላይ ያሉ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሥራ እንቅስቃሴ በመስክ በመከታተልና በየካምፓኒው ደረጃ እንዲጠናቀሩ በማማከር ኢንስቲትዩቱ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወር፣ ዘጠኝ ወር እና ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለከፍተኛ አመራሩ አቅርቦ ማስገምገም አለበት፡፡

92. ኢንስቲትዩቱ በነባር፣ ሥራ በጀመሩ እና በግንባታ ላይ ያሉ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሥራ እንቅስቃሴ በመስክ በመከታተልና በየካምፓኒው ደረጃ እንዲጠናቀሩ በማማከር ኢንስቲትዩቱ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወር፣ ዘጠኝ ወር እና ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት የሚያቀርብ ቢሆንም የኢንዱስትሪዎቹን የሥራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችለውን ሪፖርት ከማቀነባበሪያዎቹ በተከታታይ ማግኘት የሚያስችለውን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡ይህም፡- ኢንስቲትዩቱ በየዓመቱ የሚሰበስበው የሥጋ ኤክስፖርት

መረጃዎች ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ከሚሰበሰበው ጋር ሲነጻጸር የቁጥር ልዩነት ሲፈጥር ኢንስቲትዩቱ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንን ሪፖርት በመጠቀም ሪፖርት የሚያዘጋጅ መሆኑንን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

93. ስለ ሁኔታው የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ ኢንስቲትዩቱ ኢንዱስትሪዎቹ ሪፖርት እንዲያቀርቡ የሚያደርግ አስገዳጅ ሥልጣን የሌለው መሆኑን እና መረጃዎቹን ለመሰብሰብ ኢንስቲትዩቱ ጥረት የሚያደርግ ቢሆንም ገቢዎችና ጉምሩክ ከሚጠቀማቸው 'HS code' ጋር በተያያዘ ጥቂት ልዩነቶች የሚፈጠሩ ሲሆን ከዚህ አንጻር በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚፈጠሩ ሲሆን በሀገር አቀፍ ደረጃ የገቢዎችና ጉምሩክ መረጃዎችን መጠቀም እንደሚገባ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት መሆኑን እንዲሁም አንዳንዴ በራሳቸው ቁራ ሳይኖራቸው ተከራይተው የሚልኩና በገበያው ገባ ወጣ የሚሉ አካላት በመኖራቸው መሆኑን ቢገልጹም ኢንስቲትዩቱ በቅርበት ከኢንዱስትሪዎቹ ጋር በመሥራት እንዲሁም ሙያተኞቹን በማሰማራት ሪፖርቱን ማሰባሰብ የሚችል በመሆኑ መልሱ ተቀባይነት የለውም፡፡

94. ኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪዎቹን የሥራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችለውን ሪፖርት ከማቀነባበሪያዎቹ በተከታታይ ማግኘት የሚያስችለውን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ ትክክለኛ ሪፖርት እንዳይኖር እንዲሁም ሪፖርት ለማዘጋጀት የወጣው ጊዜ እና በጀት እንዲባክን ያደርጋል፡፡

## <u>በኢንስቲትዩቱ የአማካሪ ምክር ቤት መቋቋሙን በተመለከተ፡-</u>

95. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሐ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት ሊቋቋም ይገባል፡፡

96. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሐ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት ሊቋቋም አለመቻሉን ለኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ከተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

97. ስለሁኔታው የሚመለከታቸው የኢንስቲትዩቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የአማካሪ ምክር ቤቱ መቋቋም እንዳለበት የኢንስቲትዩቱ መቋቋሚያ አዋጅ ቢገልጽም ኢንስቲትዩቱ ለሌሎች ሥራ ቅድሚያ በመስጠቱ ያልተቋቋመ መሆኑን እና ለወደፊት መቋቋም እንደሚኖርበት ገልጸዋል፡፡

98. ኢንስቲትዩቱ የአማካሪ ምክር ቤት እንዲቋቋም አለማድረጉ በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራት እንዳይገመገሙ እና በግምገማው መሰረት የማስተካከያ እርምጃ እንዳይወሰድ ከማድረጉም በላይ የኢንስቲትዩቱን የመፈጸም ብቃት እንዳይጠናከር ያደርጋል፡፡

# ክፍል ሶስት

## የመደምደሚያ ሃሳቦች

ከላይ በኦዲት ግኝቶቹ ላይ እንደተመለከተው የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ በኢንስቲትዩት እና በናሙና ተመርጠው በታዩት የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎች የታዩ ግኝቶች ላይ የሚከተሉት መደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡-

99. በናሙና ተመርጠው በታዩ የሥጋ (ሃሽም/ሄልሜክስ፣ ኤልፎራ እና ሉና ቄራዎች)፣ ወተት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) እና መኖ (አዲስ ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) ማቀነባበሪያዎች ኢንስቲትዩቱ በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት በመስጠት ውጤት ማስመዝገብ አለመቻሉ፣

100. ሃሽም እና ሉና ከሁለት ዓመት በፊት እንዲሁም በመስከረም 2008 ዓ.ም አጠቃላይ በሃገሪቱ የሚገኙ የኤክስፖርት ቄራዎች በጥራት ምክንያት በሶስት ዙር ከሰባት ኤክስፖርት ቄራዎች የቀረበ 270 ቶን (1.59 ሚሊዮን ዶላር) ሥጋ በመበላሸቱ ለ6 ቀናት ከገበያ የታገዱ መሆናቸው፤

101. ወተትና የወተት ውጤቶች የጥራት ደረጃ አጠባበቅ ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ሥራ ላይ እንዲውል ክትትል አለመደረጉ እና ከወተት ማቀነባበሪያዎች የምርት ናሙና በማሰባሰብ የመጀመሪያ ደረጃ፣ ኬሚካላዊና ማይክሮባዮሎጂካዊ ጥራት ፍተሻ በማድረግ ማቀነባበሪያዎቹ እንዲያሻሽሉ ድጋፍ አለመሰጠቱ፤

102. በመኖ ምርቶች ላይ የላብራቶሪ ትንተና እንዲደረግባቸው ኢንስቲትዩቱ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት አለመሥራቱ፣

103. በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ በምርት ሂደት ባለሙያዎቹ ቀርበው እገዛ ያላደረጉ ሲሆን ባለሙያዎቹ ወደ ኢንዱስትሪዎቹ በሚሄዱበት ወቅት ስለ ምርት ሂደቱ ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በጥያቄ ስለሚያባክኑ ማቀነባበሪያዎቹ ለኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎች ያላቸው ሙያዊ አመለካከት በመቀየሩ ሙያተኞቹን ለማስተናገድ አለመቻለቸው እና በምርት ዕቅድ ላይ አብሮ አለማቀድ እና የኢንስቲትዩቱ ድርሻ ምን እንደሆነ በዕቅዳቸው ላይ የማይገለጽ እና የማይታወቅ መሆኑ፣

104. ከጥራት ጋር በተያያዘ የሥጋ እና ወተት ላብራቶሪዎች የተለየ ክፍል የሌላቸው ፣ያረጁና ጥገና ያልተደረገላቸው እና በትክክል ስለመስራታቸው ማረጋገጫ (Calibration test) ያልተደረጉ መሆኑ፣ በቂ የላብራቶሪ ፋሲሊቲ (ይህም፡- የተለየ የላብራቶሪ ክፍል፣ ኤር ኮንዲሽነር፣ ፋኖች እና ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች…)፣ የላብራቶሪ ማስኬጃ መመሪያ ወይም ማንዋል የሌላቸው፣ የላብራቶሪ ቆሻሻ መቆጣጠሪያ (residue monitoring) መሳሪያ አለመኖር እና ኢንስቲትዩቱም ሞዴል ሰርቶ ማሳያዎች እና ላብራቶሪዎችን በማቋቋም በዚሁ መሰረት እንዲስፋፋ አለማድረጉ፣

105. የወተት ማቀነባበሪያዎቹ የሰለጠነ የላብራቶሪ ባለሙያ እና መሳሪያዎች የሌላቸው በመሆኑ የማይክሮባይሎጂካል፣ አፍላቶክሲን እና ኬሚካል አናሊስስ የማያከናውኑ እና አቅራቢዎች ለወተት ባልተዘጋጀ እና ንጽህና በሌለው ዕቃ የሚያቀርቡ፣ ማቀነባበሪያዎቹ እና አቅራቢዎች ለወተት ሥራ በተዘጋጀ ተሽከርካሪ ሌሎች ዕቃዎችን የሚያጓጉዙ መሆኑ፣ ወተት ከረጅም ርቀት በማጓጓዝ የሚመጣበት ሁኔታ መኖሩ እና የተለየ እና ንጽህናውን የጠበቀ የወተት መረከቢያና መሸጫ ቦታዎች የሌላቸው መሆኑ እንዲሁም የወተት

ማቀነባበሪያዎች የወተት ማሰባሰቢያና ማቀዝቀዥ ማዕከል እንዲያቋቁሙ ድጋፍ አለመደረጉ ፤

106. በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ለተሰማሩ ባለሃብቶች ኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት ድጋፍ የማያደርግላቸው መሆኑ፣

107. የሥጋ ኢንዱስትሪዎች የዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟሉ ምርቶች ለሃገር ውስጥና ለዓለም ገበያ በስፋት ማቅረብ አለመቻላቸው፤ይህም በናሙና ተመርጠው የታዩ የሥጋ ኢንዱስትሪዎች (ሉና፣ ሂልሚክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ ደ/ዘይት እና አክሽከር ኤክስፖርት ቄራዎች) አፈጻጸም ከዓመት ዓመት እየቀነሰ የሚሄድበት ሁኔታ መስተዋሉ ለዘርፉ ስጋት መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ የ2005 ዓ.ም እና 2006 ዓ.ም የአፈጻጸም ሪፖርቶች ለመረዳት መቻሉ፣

108. ኢንስቲትዩቱ ከ2005- 2008 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ ያሉ ችግሮችን በመለየት ሊለሙ የሚችሉ ወጪ ቆጣቢ፣ ምርትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ እና የምርት ጥራትን ሊያስጠብቁ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች እንዲሸጋገር በማድረግ ኢንዱስትሪዎቹም የራሳቸውን የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ ሊደግፍ አለመቻሉ፣

109. ስጋን በገፈፋ (carcass) መልክ ከመላክ ይልቅ በተቆራረጠ መልኩ ሊላክ የሚችልበትን የማቀነባበር ሥርዓት አለመዘርጋት ፣ ከደጋውና ወይናደጋው የሀገሪቱ ክፍል ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚቀርቡት እንስሳት ሥጋ ቶሎ የመጥቆር ባህሪ ያለው በመሆኑ የሥጋ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች የቆላ ሥጋን ብቻ ለኤክስፖርት መጠቀማቸው ለዘርፉ ከፍተኛ ሥጋት ሆኖ እያለ በምርምር መፍትሄ መስጠት አለመቻሉ እንዲሁም ጠንካራ ሥጋን ማለስለስ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ቢኖሩም ይህን ለመተግበር የሚያስችል ቴክኖሎጂና ሥልጠት ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ፣

110. ወተትና ወተት ውጤቶች ጥራትና ቁጥጥር እንዲሁም ደህንነት ማረጋገጫ ላይ ምርምር ማካሄድ አለመቻሉ ፣ በፍየል ወተት ላይ ጥናት አለመደረጉ እና ወተትን ለረጅም ጊዜ ማቆየት የሚያስችል ማሽኖችን እንዲጠቀሙ አለማድረግ (long shelf life machine/UHT/) እንዲሁም በኬሚካል ወተትን የማቆየቱ ሂደት ጠቀሜታውና ጉዳቱ ተለይቶ ለማቀነባበሪያዎቹ ሳይንሳዊ የሆነ ጥናት እንዲሰጣቸው አለመደረጉ፣

111. በናሙና ተመርጠው በታዩ አራት የሥጋ (ሉና፣ ሄልሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ ደ/ዘይት እና ጅጅጋ ላይቭስቶክ ኤክስፖርት ቄራዎች) ፣ አምስት የወተት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) እና ሁለት የመኖ (አዲስ አለም ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ታዳሽ የኃይል ምንጮችን የማይጠቀሙ እና የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎች ያልተሸፈኑና (Safety tank) የሌላቸው መሆኑ፣

112. ለኢንዱስትሪዎች ከፍተኛ ችግር ሆኖ የሚታየውን የመብራት መቆራረጥ በተወሰነ ደረጃ ማቃለል የሚችለውን ባዮጋዝ እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ በናመና ተመርጠው በታዩ ኢንዱስትሪዎች ላይ እንዲገነቡ እገዛ አለማድረጉ፤ ይህም አልሚ ትኩስ ወተት ማቀነባበሪያ የባዮ ጋዝ ቴክኖሎጂ እና ውሃን መልሶ አጣርቶ ለመጠቀም የሚያስችል ቴክኖሎጂን ለመጠቀም በዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ የሚያደርግለት እገዛ የሌለ መሆኑ፣

113. በናሙና ተመርጠው በታዩ ሁሉም የሥጋ (ሉና፣ ሄልሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ ደ/ዘይት እና ጅጅጋ ላይቭስቶክ ኤክስፖርት ቄራዎች)፣ ወተት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ጄኔሲስ ፋርም፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) እና መኖ (አዲስ አለም ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ወቅታዊ የቴክኒክ ፍተሻ የሚያካሂዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ፣

114. የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ዕቅድ ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ አካል ጉዳተኞችን...) ባካተተ መልኩ ታቅዶ በዕቅዱ መሠረት አፈጻጸሙን ያካተተ ሪፖርት ማግኘት አለመቻሉ፣

115. ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶችን በሃገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ የሚያስችል ስልት ኢንስቲትዩቱ ቀይሶ ተግባራዊ አለማድረጉ፣

116. በወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሃገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት በመያስችል (Import substitution) ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ እንዲችሉ አለመደረጉ እና ከ2005- 2007 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የወተትና ወተት ውጤቶች ኤክስፖርት ዕቅድ አለመያዙ ለዘርፉ ትኩረት አለመሰጠቱን የሚያመለክት ሲሆን የ2006 ዓ.ም የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ድርጅትታዊ መዋቅርና የሰው ሃይል ዕቅድ ማስረጃ እንደሚያመለክተው በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ 44,604,941.56 ዶላር የሚያወጣ 17 ዓይነት ምርት ወደ ሃገር ውስጥ መግባቱን እና ይህም ወጪ በዓመት ሲሰላ 8,920,988.31 ዶላር እንደሚሆን እንዲሁም ወደ ሃገሪቱ የሚገባው የወተትና ወተት ውጤቶች አማካይ ዕድገቱ 35.95% እንደሆነ ያሳያል፤ በተጨማሪም አሁን በ2007 ዓ.ም የገበያ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በ20 ሚሊዮን ዶላር በዓመት ወተት ከውጭ ሃገር ወደ ሀገራችን የሚገባ መሆኑን የሚያስረዳ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ይህን ወጪ ለመቀነስ የሚያስችል ድጋፍ ለማቀነባበሪያዎቹ መስጠት አለመቻሉ፣

117. የሀገራችን የሥጋ ማቀነባበሪያዎች በተወሰኑ አይነት (በፍየል እና በግ) ሥጋ ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በሌሎች የተቀነባበረ የፍየል፣ በግ፣ ዳልጋ ከብት እና ግመል ወ.ዘ.ተ ሥጋ ላይ ትኩረት አድርገው

የማይሠሩ መሆኑን እንዲሁም በሙሉ አቅማቸው እንዳይሰሩ ለእርድ የሚቀርቡ እንስሳት ኤክስፖርት ቄራዎች በሚፈልጉት ዓይነት፣ ዕድሜ፣ ክብደትና ዋጋ እንዲቀርብ ክትትል አለመደረጉ እንዲሁም ብዛትን አስመልክቶ የሥጋ እና ወተት ማቀነባበሪያዎቹ የማምረት አቅም ያላቸው ቢሆንም በሙሉ አቅማቸው እያመረቱ አለመሆኑ፣

118. የሀገራችን የወተት ማቀነባበሪያዎች በተወሰኑ አይነት (ፓስቸራይዝድ ወተት፣ እርጎ፣ አይብ፣ የገበታ ቅቤ እና የምግብ ቅቤ) ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ ሲሆን በሌሎች ክሬም፣ የተፈጨ ቺዝ፣ ፕሮቫለን ቺዝ፣ ሞዞሬላ ቺዝ፣ ፌታ ቺዝ፣ እስሞክድ ቺዝ፣ ፎንቲና ቺዝ ወ.ዘ.ተ ላይ ትኩረት እድርገው የማይሠሩ መሆኑ፣

119. ኢንስቲትዩቱ በእንስሳት ምርቶች ላይ የሚካሄዱ የንግድ ትርኢቶች እና ባዛሮች በጥናት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ የማያደርግ እና ውጤታቸውንም የማይለካ መሆኑ፣

120. የአፍሪካ ላይቭስቶክ ኤግዚቢሽን እና ኮንግረንስ (ከሚያዚያ 30/2006 ዓ.ም እስከ ግንቦት 02/2006 ዓ.ም) በሚሊኒየም አዳራሽ በተካሄደው ላይ የውጪ ገዥዎችን በኤግዚቢሽን እንዲሳተፉ በማስተዋወቅ ደረጃ ውስንነት እንደነበረ፣ Ethio Api Expo በአዲስ አበባና Veterinary Conference በመቀሌ በተመሳሳይ ጊዜ የተካሄደ መሆኑ እና የተጠበቁ ህዝባዊ ድርጅቶችና የክልል ቢሮዎች አለመሳተፋቸው የኤግዚቢሽኑን ውጤታመነት የቀነሱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ መቻሉ፣

121. በወተት እና ሥጋ ምርቶች ላይ የሚካሄዱ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮች በጥናት ላይ ያልተመረኮዙ እና ሁሉንም የወተት እና ሥጋ ማቀነባበሪያዎች ያላሳተፉ እንዲሁም ውጤታቸው የማይለካ መሆኑ፣

122. ኢንስቲትዩቱ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ኢንዱስትሪዎቹን ከጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች እና ከውጭ ሃገር ገዥዎች ጋር በዘመናዊ የግብይት ሥርዓት የማስተሳሰር ሥራ ሊያከናውን አለመቻሉ፣

123. ለኤክስፖርት ቄራዎች እንስሳት የሚያቀርቡ ማህበራትና ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችና ነጋዴዎችን በመለየት ከቄራዎች ጋር ማስተሳሰር አለመቻሉ፣ አሁን ያለው የሥጋ ኤክስፖርት ገበያ በደንበኞች ትዕዛዝ እና ቄራዎች በራሳቸው መንገድ ገበያን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ እንጂ ኢንስቲትዩቱ በሌሎች ሀገራት ያለውን አማራጭ መዳረሻ ገበያዎችን በራሱና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት (ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር እና ኢምባሲዎች) ጋር በመሆን ገበያ ማፈላለግ አለመቻሉ፣

124. በበረዶ የቀዘቀዘ የዳልጋ ከብት ሥጋን መግዛት ወደ ሚፈልጉ ሀገሮች አንጎላ፣ ግብጽ፣ ቻይና፣ ኢራን፣ አልጄሪያና ሞሮኮ ገበያዎች መግባት አለመቻሉን ፣በገዥ ሀገራት በሚደረጉ የምርት ማስተዋወቂያ መድረኮች ላይ የእንስሳት ምርት ላኪዎች ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ የሚጋብዝ ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ እና የሥጋ መዳረሻ ገበያዎችን የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦት ዙሪያ የደሰሳ ጥናቶችን በማከናወን መረጃዎችን በማጠነቀር ቄራዎች እንዲደርሳቸው አለማድረጉ፣

125. የወተት አቅርቦት ችግር እና በጾም ወቅት የሚፈጠረው የገበያ እጥረት ከፍተኛ በመሆኑ ባለሃብቱ በሥራው እምነት እንዲያጣ እያደረገ መሆኑ እንዲሁም ሱማሌ እና ጅቡቲ አከባቢ ከፍተኛ የወተት ፍላጎት ያለ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ የአከባቢዎቹን ፍላጎት በመለየት ማቀነባበሪያዎቹን ሊደግፍ አለመቻሉ እንዲሁም የወተት ዘርፉ የወጪ ምርቶች የገበያ እስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን የኢንስቲትዩቱ የ2007 ዓ.ም ዕቅድ የሚያመለክት ሲሆን በተለይ በአሁኑ ወቅት ከአፍላቶክሲን ጋር በተያያዘ የማቀነባበሪያዎቹ የገበያ ሁኔታ የተቀዛቀዘ መምጣቱ ለዘርፉ ስጋት ሲሆን

በተለይ በአዳማ አከባቢ የሚገኘው ያቅላ ወተት ማቀነባበሪያ ከገበያ ለመውጣት የተገደደ መሆኑ፣

126. ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎች ኢንቨስትመንት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን አቅርቦት እጥረት መንስኤዎች በመለየት በአቅርቦት ዘርፍ ከተሰማሩ ባለሃብቶችና ተቋማት ጋር ለማስተሳሰር የሚያስችል ደሰሳ ጥናት (Supply chain) በማካሄድ ተግባራዊ እንዲሆን  አለመደረጉ፣

127. የማሽኒያ፣ የኬሚካል፣ የላብራቶሪ መሳሪያዎች…፣ የቁም እንስሳት አቅርቦት በተለይ በሥጋና ወተት ፍላጎትና እንስሳት አቅርቦት ላይ ደሰሳ ጥናት በማከናወን ለማቀነባበሪያዎቹ አለመሰራጨቱና ተግባራዊ እንዲደረግ አለመደረጉ፤ በተጨማሪ የእንስሳት አቅርቦትን ችግር ለመፍታት የግል ባለሃብቶችና የቄራ ባለቤቶች መሬት ወስደው የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል እንዲያረቡ እና እንዲያደልቡ ብሎም ከይዞታቸው ለእርድ እንዲያቀርቡ የእንስሳት እርባታ (ራንች) እንዲያቋቁሙ አለመደረጉ፣

128. ለመኖ ማቀነባበሪያ ግብዓትነት የሚያገለግሉ የፋብሪካ ተረፈ ምርቶች ለተደጋጋሚ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተጋለጡ በመሆናቸው የዋጋ ጭማሪ እየተስተዋለባቸው መሆኑን እንዲሁም ማቀነባበሪያዎቹ በቂ ገበያ ያለማግኘት እና ለሥራው የሚያስፈልግ የሰው ኃይል ከሚሟላት ይልቅ በተወሰነ ባለሙያዎች ብቻ ሥራን የሚያከናውኑ መሆኑን በወንጂ ሸዋ እና መተሃራ ስኳር ፋብሪካ ዙሪያ የማደለቢያ ጣቢያዎች እና የመኖ ልማት ትስስር የመስክ ሪፖርት 2006 ዓ.ም እና በናሙና ተመርጠው ከታዩ ሁለት (አለማ ካዎዳይስ እና አዲስ አለም ሞጆ) የመኖ ማቀነባበሪያዎች በኦዲቱ ወቅት በቀረበላቸው መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፤

129. የዳበረ ልምድ ካላቸው ሀገራት በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም እና በሥጋ ሎጂስቲክ አመራር ላይ ኢንስቲትዩቱ ለኢንዱስትሪዎቹ ድጋፍ ማድረግ አለመቻሉ፣

130. ኢንስቲትዩቱ በኢንዱስትሪዎቹ ለሚከሰተው የመሣሪያዎች ብልሽትና የመለዋወጫዎች ችግር አስመልክቶ የሥልጠና እና ድጋፍ አገልግሎት አለመስጠቱን እንዲሁም ከኢንስቲትዩቱ ለሥራ ተልከው ወደ ኢንዱስትሪዎቹ የሚሄዱ ባለሙያዎች በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም ላይ እገዛ ለማድረግ የሚያስችል በቂ የተግባር ክህሎት የሌላቸው መሆኑን እና ኢንስቲትዩቱ የእንስሳት ውጤቶች በመዳረሻ ሀገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን በመለየት ለኢንዱስትሪዎቹ ያላስተዋወቀ እና ማስረጃውን ያልሰጣቸው/ያላሰራጨ መሆኑ፣

131. በኢንስቲትዩቱ 165 ዓይነት ንብረቶች ውሳኔ ያላገኙ እና ጥቅም ላይ የማይውሉ፣ 2 ተሽከርካሪዎች እና 8 የእርሻ መሳሪያዎች ውሳኔ ያገኙ ነገር ግን ያልተወገዱ እንዲሁም 81 ዓይነት ንብረቶች/መሣሪያዎች ያረጁና የተበላሹ መሆኑን እንዲሁም 9 ዓይነት የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸውና ጥቅም ላይ የማይውሉ ኬሚካሎችና የወተት ላብራቶሪ መሳሪያዎች መኖራቸውን ከማስረጃዎች ለመረዳት መቻሉ፣

132. .በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎች ያልተዘጋጁና ያልተሰራጩ እንዲሁም ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች ጠቋሚ ጥናት በማድረግ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማደረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሰጥ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አለመደረጉ እና በአፈጻጸም ወቅት ለተከሰቱ ችግሮች ስለተሰጠው የማስተካከያ እርምጃ የሚያመለክት ማስረጃ በናሙና በታዩት ማቀነባበሪያዎች ተጠይቆ ማግኘት አለመቻሉ፣

133. ኢንቨስትመንቱ እንዳይስፋፋ እንቅፋት የሚሆኑ ችግሮች በአፋጣኝ መፍትሄ የማይሰጣቸው መሆኑ፤ ለምሳሌ፡- በናሙና ተመርጠው የታዩት አራቱ የሥጋ፣

ስድስቱ የወተት እና ሁለቱ የመኖ ማቀነባበሪያዎች እንደገለጹት የመብራት መቆራረጥ በቀን ከብር 10,000 እስከ 15,000 የነዳጅ ወጪ እንደሚያስወጣቸው እና ለመሳሪያዎች ብልሽት እየዳረጋቸው መሆኑን እንዲሁም ከማስፋፋት ጋር በተያያዘ የራሳቸው እንስሳት ማቆያና ማደለቢያ እንዲኖራቸው የሚጠይቁትን መሬት የማያገኙ መሆኑን እና በልማት ባንክ በኩል ለዘርፉ ትኩረት ባለመስጠት የሚሰጣቸው ብድር የሚጓተትበት ሁኔታ መኖሩ፣

134. አልሚ ትኩስ ወተት የራሱ የሆኑ 27 የወተት ላሞች ያሉት ቢሆንም ከማቀነባበሪያው ቦታ ከ100 ኪ.ሜ በላይ ርቀት ባለው ቦታና በመኖሪያ አከባቢ የሚያረቡበት ሁኔታ መኖሩን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ መቻሉ፤ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ ብዙ ጊዜ በመድረክ ሰብስቦ በመወያየት መረጃን በማሰባሰብ ከመርካት ይልቅ የኢንስቲትዩቱ ባለሞያዎች ማቀነባበሪው ድረስ በመሄድ አብሮ መስራት አለመቻላቸው፣

135. አደአ የወተት ህብረት ሥራ ማህበር የተመጣጠነ የእንስሳት መኖን በቀን በሶስት ጊዜ ፈረቃ ከ750 ኪ.ግ በላይ ማቀነባበር የሚያስችለው መሳሪያ ያለው ቢሆንም እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት የሰጠ አለመሆኑ እና ኢንስቲትዩቱ ይህን ዘርፍ ከማስፋፋት እና ውጤታማ ከማድረግ አኳያ የማቀነባበሪያውን ችግር በመለየት ማቀነባበሪያው ወደ ሥራ እንዲገባ ተገቢውን እገዛ ማድረግ አለመቻሉ፣

136. ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎችን ለይቶ ተሞክሮዎቹን አቀናብሮ ለማቀነባበሪያዎቹ በማሰራጨት ተግባራዊነቱን የማይከታተል መሆኑ፣

137. በኢንስቲትዩቱ የተቀናበሩና የተሰራጩ መልካም ተሞክሮ ሰነዶች ኢንዱስትሪዎቹ በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸው እና የኢንስቲትዩቱ ባለሙያዎችም ወደ ውጪ ሃገር ሄደው ከመጡ በኋላ

ለማቀነባበሪያዎቹ ስላዩቸው ተሞክሮዎች ያገኙትን ልምድ የማያካፍሉዋቸው መሆኑን በናሙና ተመርጠው የታዩት ሶስት የሥጋ (ሂልሜክስ/ሃሸም፣ ኤልፎራ እና ሉና) ፣ ስድስት የወተት (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ጄኔሲስ ፋርም፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) እና ሁለት የመኖ (አዲስ አለም ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች መግለጻቸው፣

138. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያና ሌሎች መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በመተንተን እና በማደራጀት ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጩ ሊያደርግ አለመቻሉ፤ ይህም፡- ኢንስቲትዩቱ የውጭ ገበያ መረጃዎችን በማሰባሰብ በመተንተን እና አደራጅቶ በመያዝ ለተጠቃሚዎች በማሰራጨት እና የወጪ ምርቶች የገበያ እስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉን የኢንስቲትዩቱ የ2007 ዓ.ም ዕቅድ ያመለክታል፤ እንዲሁም እስከ አሁን በኢንስቲትዩቱ ስለተሰራጩ መረጃዎች ከማቀነባበሪያዎች እና በአከባቢው የሚገኙ የከተማ ኢንዱስትሪ የሥራ ሂደቶች በኦዲቱ ወቅት ተጠይቀው ማቅረብ አለመቻላቸው፣

139. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የሚውሉ የኢንቨስትመንት ቦታዎችን በዝርዝር ለይቶ እንዲታወቁ በማድረግ መረጃውን በዳታ ቤዝ በማጠናቀር ለባለሃብቶች በቀላሉ መስጠት አለመቻሉን በናሙና ተመርጠው ከታዩት የሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ለመረዳት መቻሉ፣

140. ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ የሚገኙትን የክልሎች የወተት ሃብት(Milk Shed)ና የመኖ የማምረት አቅም እንዲሁም የእንስሳት አቅርቦት መጠን በመለየት መረጃዎችን ማደራጀት አለመቻሉ እና የእንስሳት ዱካን (Tracibility) ለመመዝገብ የሚያስችል መዝገብ (records) ተግባራዊ እንዲደረግ በማድረግ የእንስሳት ጤና ሥርዓትና ቁጥጥርን አስመልክቶ መረጃዎችን ለተቀባይ ሀገራት የማድረስና የማስተዋወቅ ሥራ አለመከናወኑ፣

141. ኢንስቲትዩቱ ሁሉንም ክልሎች በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ተሳታፊ ማድረግ አለመቻሉ፤ ይህም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች፣ ሶማሌ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና የትግራይ ክልሎች በዘርፉ ትኩረት ያልተሰጣቸው መሆኑን ለእንስሳት ሀብት ልማት ኢንቨስትመንት የሚውሉ መሬቶች ለመለየት በክልሎች በተደረገ ጥናት የመስክ መልስ ሪፖርት 2004 ዓ.ም ለመረዳት መቻሉ፤ እንዲሁም ጅጅጋ ፊቅ አከባቢ ከፍተኛ የፍየል አቅርቦት ያለ ቢሆንም ኢንስቲትዩቱ ለክልሉ ትኩረት በመስጠት በአከባቢው የሚገኙትን አቅራቢዎች ከኢንዱስትሪዎቹ ጋር የማስተሳሰር ሥራዎችን ያላከናወነ መሆኑን በጅጅጋ ክልል የኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ለበላይ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ከቀረበላቸው መጠይቅ ለማወቅ መቻሉ፣

142. ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት ወደ ሥራ እንዲገቡ ሊያደርግ አለመቻሉ፣ ይህም አሽራፍ ኤክስፖርት ቄራ በባህርዳር ከተማ በ5.5 ሄ/ር ላይ አሽራፍ በተባለ ሱዳናዊ ባለ ሃብት ከ9 ዓመት በፊት ግንባታው ተጀምሮ በ2002 ዓ.ም የተመረቀ ሲሆን ቄራው እጅግ ዘመናዊና በቀን 2700 በግና ፍየል እንዲሁም 540 የዳልጋ ከብት የማረድ አቅም ያለው ቢሆንም ቄራው በ2004 ዓ.ም በበረዶ የቀዘቀዘ የዳልጋ ከብት ሥጋ መላክ ጀምሮ ያቋረጠ እና ከገበያ ውጪ መሆኑን እና አበርገሌ ኤክስፖርት ቄራ በመቀሌ ከተማ በ3 ሄ/ር መሬት ላይ በትግራይ መልሶ ማቋቋም ድርጅት ተገንብቶ በ2002 ዓ.ም ሥራ የጀመረ ዘመናዊ ቄራ ሲሆን ቄራው 950 በግና ፍየል እንዲሁም 240 ዳልጋ ከብት በቀን የማረድ አቅም ያለው እና የቀዘቀዘ የዳልጋ ከብት ሥጋ ኤክስፖርት ሲያደርግ ቆይቶ ከዓመት በፊት ከገበያ ውጪ የሆነ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ መቻሉ፣

143. ኢንስቲትዩቱ በተለይም በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር ውጤታማ የምርት የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖራቸው በማድረግ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ማድረስ አለመቻሉ፤ እንዲሁም የህብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው አቅማቸውን በማሳደግ የእርድ እንስሳት እና ወተት እንዲያቀርቡ በየደረጃው ካለው ህብረት ሥራ ማህበራት አደራጅ መ/ቤቶች ጋር በጋራ እንዲሰራ አለመደረጉ፣

144. በኢንስቲትዩቱ የሚሰጡ ሥልጠናዎች በደሰሳ ጥናት (need assessment) ላይ የተሞረኮዙ እና ወቅቱን የጠበቀ አለመሆኑን ከሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያዎች የበላይ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ መጠይቅ ለማወቅ ስለመቻሉ፤ ይህም ሥልጠናው የሥጋ እና የወተት ገበያ በቀዘቀዘ ወቅት (ሥጋ ወደ አረብ ሀገራት የሚላክ በመሆኑ ከሙስሊም በዓላት ውጪ እና ወተት በሀገር ውስጥ የሚሸጥ በመሆኑ በጾም ወቅት) ላይ ብቻ የማይሰጥ በመሆኑ ጉዳዩ በቀጥታ የማይመለከታቸውን ባለሙያ ለመላክ የሚገደዱ መሆኑ፣

145. ኢንስቲትዩቱ የትምህርት፣ ሥልጠና፣ የምርምር ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር ፎረም ከ2 ዓመት በፊት ያቋቋመ ቢሆንም በቀጣይነት ለመተግበር የሚያስችለው መመሪያ ወይም ማንዋል አዘጋጅቶ ወደ ሥራ ሊገባ አለመቻሉ፤ ይህም በዘርፉ የአገር ውስጥ ምርምር አቅም እንዲጠናከር እና የዘርፉን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎትን ለማሟላት በኢንዱሰትሪዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በጋራ የተከናወኑ ተግባራት አለመኖሩን በናሙና ተመርጠው በታዩ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች ከቀረቡ መጠይቆች ለመረዳት መቻሉ፤ እንዲሁም የትስስር ፎረሙ ለማቀነባበሪያዎቹ ያለው ጠቀሜታ አነስተኛ መሆኑን እና የወደፊት ጠቀሜታውን ባለመረዳታቸው ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስቸግር መሆኑን በናሙና ተመርጠው የታዩት ስድስቱ (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣

ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት)፣ አራቱ የሥጋ ፋብሪካዎች (ሄልሜክስ/ሃሽም፣ ኤልፎራ፣ ሉና እና ጅጅጋ ላይቭስቶክ) እና ሁለቱ የመኖ (አዲስ አለም ሞጆ እና አለማ ካዋዳይስ) መግለጻቸው፤

146. ኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪዎቹን የሥራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችለውን ሪፖርት ከማቀነባበሪያዎቹ በተከታታይ ማግኘት የሚያስችለውን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ አለማድረጉ፤ይህም፡- ኢንስቲትዩቱ በየዓመቱ የሚሰበስበው የኤክስፖርት መረጃዎች ከገቢዎችና ጉምሩክ ከሚሰበሰበው ጋር ሲነጻጸር የቁጥር ልዩነት ሊፈጥር መቻሉን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች ለመረዳት መቻሉ፤

147. ኢንስቲትዩቱ በወተት ዘርፍ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የግል ተቋማት መካከል ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ አለማድረጉ፤ ይህም የወተት ማቀነባበሪያዎች ማህበር ከዚህ በፊት በ2003 እና በ2005 ዓ.ም ተቋቁሞ የፈረሰ ሲሆን በ2006 ዓ.ም እንደገና የተቋቋመ ቢሆንም ማህበሩ በተጠናከረ ሁኔታ ወደ ተግባር መግባት አለመቻሉን በናሙና ተመርጠው የታዩ ስድስቱ (ሆላንድ ዴይሪ፣ አደአ ወተት፣ ጄኔሲስ ፋርም፣ አልሚ ትኩስ ወተት፣ ኤሌምቱ ወተት እና ያቅላ ወተት) ማቀነባበሪያዎች የገለጹ ሲሆን በሀገሪቱ ወደ 34 የሚሆኑ የወተት ማቀነባበሪያዎች ቢኖሩም እስከ 21/04/2008 ዓ.ም ድረስ የማህበሩ አባል መሆን የቻሉት 16 ማቀነባበሪያዎች ብቻ መሆናቸውን ማቀነባበሪያዎቹ መግለጻቸው፤ በመሆኑም ኢንስቲትዩት ማህበሩን በማጠናከር እና ሁሉንም ማቀነባበሪያዎች ተሳታፊ በማድረግ ማህበሩ ወደ ተግባር እንዲገባ ሊያደርግ አለመቻሉ፣

148. ኢንስቲትዩቱ የሚሰጠውን ድጋፍ ተደራሽ ለማድረግ በክልሎች የራሱ መዋቅር በተዋረድ የሌለው ቢሆንም በኢንዱስትሪዎቹ አከባቢ ከሚገኙ እና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው በከተማ መስተዳድር የንግድና ኢንዱስትሪ የሥራ ሂደቶች፣ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች እና ከእንስሳት ሃብት ልማት ኤጀንሲዎች ጋር በቅንጅት አለመስራቱ፣

149. ኢንስቲትዩቱ በወጪ ንግድ ሂደት ውስጥ የሚታዩ ማነቆዎችን ለመፍታት ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር፣ ከባንኮች፣ ከጉምሩክ፣ ከአየር መንገድ፣ ከግብርና ሚ/ር እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ለመሥራት እና ለመከታተል እንዲሁም ችግር ሲገጥም መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል መድረክ/ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለመቻሉ እንዲሁም ኢንስቲትዩቱ የኮልድ ቼይን ሰንሰለት ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ከቄራዎች፣ ከአየር መንገድ፣ ከኤርፖርቶች ድርጅትና ከትራንስፖርት ሚ/ር ጋር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በመዘርጋት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርሞ በሰነዱ መሰረት ወደ ተግባር ሊገባ አለመቻሉ፣

150. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሐ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት ሊቋቋም አለመቻሉ፣

151. በአጠቃላይ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሁለገብ ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥርዓት አፈጻጸም ላይ ከባለድረሻ አካላት ጋር በቅንጅት አለመሰራቱ እና ከአቅርቦት ሥርዓት (Production) ይልቅ የማቀነባበር ሂደት (Production) ላይ ትኩረት በመስጠት አለመስራቱ ከላይ የተጠቀሱት ግኝቶች እንዲፈጠሩ አስችሏል፡፡ ስለሆነም የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት በማቀነባበር ላይ የሚሰራ ቢሆንም አቅርቦት እና የገበያ ሥርዓት ላይ በቅንጅት ጥራት ማስጠበቅ እና አለም አቀፍ ገበያ መግባት ካልቻለ ምንም የማቀነባበሩ ሂደት ቀልጣፋ ቢሆንም እንኳን ጥራት ያለው የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ምርት በአለም አቀፍ ገበያ አቅርቦ ተወዳዳሪ ማድረግ ስለማይቻል ሀገሪቷ ከኢንደስትሪው የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ያቀደችውን ግብ በተሟላ መልኩ እንዳይሳካ እንቅፋት ሊሆን ስለሚችል ከላይ የተጠቀሱትን ድክመቶች እና ግድፈቶች በብቃት፣ ኢኮኖሚ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ የኢንስቲትዩቱን ሁለገብ ድጋፍ

አሰጣጥና ቴክኖሎጂ ሽግግር ሥርዓት ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲተገበሩ ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

## ክፍል አራት

## <u>የማሻሻያ ሃሳቦች</u>

152. ለሀገሪቷ እድገት የኢንዱስትሪው ዘርፍ የአንበሳውን ድርሻ የሚይዝ መሆኑን የኢንስቲትዩቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የሚያመለክት ሲሆን ይህንን የኢንዱስትሪ ዕድገት ግብ ለማድረስ ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና ጥራት ቁጥጥር በማድረግ ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟላ ምርት ለሃገር ውስጥና ለዓለም ገበያ እንዲያቀርቡ መደገፍ ይጠበቅበታል፡፡

153. በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበር ላይ የተሰማሩ ኢንዱስትሪዎችን አቅም ለማሳደግ እና በዘርፉ የሚመጡትን ቴክኖሎጂዎች በአፋጣኝ ወደ ተግባር ለማስገባት ይቻል ዘንድ ኢንስቲትዩቱ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ማቀነባበር ላይ ለተሰማሩ ባለሃብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና ሙከራ ምርት ድጋፍ ማድረግ አለበት፡፡

154. ኢንዱስትሪዎቹ የዓለም አቀፍ ጥራትን የሚያረጋግጥ የማቀነባበር ሂደት፣ ቀልጣፋ አመራር ለመፍጠር፣ ፕሮግራሞችን ተግባራዊ ለማድረግ በዘርፉ ኢንዱስትሪ ውስጥ የቴክኖሎጂ፣ ዕውቀት እና ክህሎት ሽግግር እንዲኖር ኢንስቲትዩቱ በሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት፣ ኢንዱስትሪዎቹ የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ በማድረግ እና የውጭ ባለሃብቶች በዘርፉ እንዲሳተፉ በማድረግ ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን ወደ ኢንዱስትሪዎች ሊያሸጋግር እና ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡

155. በኢንዱስትሪ ልማት ዘርፉ በተለይም ለሴቶችና ወጣቶች የሥራ እድል እንዲፈጠር ብሎም ሀገሪቷን በዘርፉ ተወዳዳሪ ማድረግ እንዲቻል የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎች ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ

አቅርቦት ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (Cross Cutting Issues) ያካተቱ ሊሆን ይገባል፡፡

156. ኢንስቲትዩቱ የሚመደብለትን በጀት በአግባቡ ለታቀደለት ዓላማ ብቻ ማዋል እንዲችል በኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሚመለከቱ ሥራን ለማካሄድ በዕቅድ የተገዙ ንብረቶች/መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸው/የማይሰሩት (Expired/ Damaged) የሆኑት የሚወገዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

157. ለሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎች ምርት አስተማማኝ የመዳረሻ ገበያ ለመፍጠር ኢንስቲትዩቱ የዳበረ ልምድ ካላቸው ሀገራት በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም፣ በሥጋ ሎጅስቲክስ አመራርና ግብይት ዙሪያ በእንስሳት ምርቶች ላይ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮችን በማዘጋጀት በገዥ ሀገራት በሚደረጉ መድረኮች ላይ በማስተዋወቅ እና በመዳረሻ ሃገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን እንዲሁም የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦትን በመለየትና እንዲሚሉ በማድረግ ለማቀነባበሪያ ፋብሪካዎቹ ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል፡፡

158. ኢንስቲትዩቱ ለዘርፉ ማደግ ዋናው የግብዓት ምንጭ መሆኑን ተገንዝቦ ለዘርፉ የግብዓት አቅርቦት በዓይነት በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱሰትሪዎች እንዲለሙ ሊደግፍ፣ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም ዓቀፍ ገበያ በምርቶች እሴት ሰንሰለት በዘርፉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ሊያደርግ እንዲሁም በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪ ምርቶች ፍላጎትና አቅርቦት (Supply Chain) ላይ የደሰሳ ጥናት በማካሄድ ኢንዱስትሪዎቹን ሊደግፍ ይገባል፡፡

159. ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ዘርፍን ለማሳደግ እና በዘርፉ በመሳተፍ ላይ ያሉትን ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን አቅም ለማጎልበት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት(በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች፣ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር ከሚገኙ የግልና የመንግስት ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ግብርና ሚ/ር፣ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ክልሎች፣ አየር መንገድ፣ ኤርፖርቶች ድርጅት እና ትራንስፖርት ሚ/ር) ጋር በመቀናጀት መስራት ይኖርበታል፡፡

160. ኢንስቲትዩቱ በሥጋና ወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት በሚያስችል (import substitution) ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ መቅረብ እንዲችሉ በማድረግ ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶች በአገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ ሊያደርግ ይገባል፡፡

161. በዘርፉ ኢንቨስትመንት አዳዲስ ባለሃብቶች እንዲሳተፉ እና የምርት ኤክስፖርት መጠን እንዲያድግ ኢንስቲትዩቱ የሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎችን ሊያዘጋጅና ሊያሰራጭ፣ ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሃብቶች ጠቃሚ ጥናት ሊያደርግ፣ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሰጥ፣ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሊያካሂድ እና በዘርፉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማነቆዎች እንዲወገዱ ድጋፍ በመስጠት አዳዲስ ባለሃብቶች በዘርፉ በብዛት እንዲሰማሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡

162. ኢንዱስትሪውን ለመደገፍ እና የኢንዱስትሪዎቹን ዕውቀትና ክህሎት ለማሳደግ በሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎች ተለይተው ተሞክሮዎቹ ተቀናብረው

በኤክስፖርት ቄራዎች፣ ወተትና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ተግባራዊ (implement) ሊደረጉ ይገባል፡፡

163. በሥጋ፣ ወተት እና መኖ ዘርፍ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሃብቶች በስፋት እንዲሳተፉ እና በኢንስቲትዩቱ የተጠናከረ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት እንዲኖር ለማደረግ ኢንስቲትዩቱ ለሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያ፣ ለኢንቨስትመንት ሊውሉ የሚችሉ ቦታዎችን ዝርዝር፣ የክልሎችን የእንስሳት አቅርቦት መጠን፣ የወተት ሃብትና የመኖ ማምረት አቅምና ሌሎች መረጃዎች በማሰበሰብ፣ በመተንተን እና በዳታ ቤዝ በማደራጀት ለተጠቃሚዎች በቀላሉ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

164. በዘርፉ ጥራት ያለው ምርት ገዥዎች ጋር እንዲደርስ በማድረግ የተጠቃሚውን ፍላጎት በማስጠበቅ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ለማግኘት ይቻል ዘንድ ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት ወደ ሚላኩባቸው መዳረሻ ገበያዎች እስኪደርሱ ድረስ ሱፐርቪዥን ሥራ በማድረግ ለቄራዎች እና ለወተት ማቀነባበሪያዎች ግብረ- መልስ በመስጠት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበሩ በማድረግ የማቀነባበሪያዎቹን አፈጻጸም ሊያሳድግ ይገባል፡፡

165. ኢንዱስትሪዎቹ ወደ ምርት ማምረት እንዲገቡ እና ዘርፉን ማሳደግ እንዲችሉ ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታ ያልጀመሩ፣ ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየትና የገጠማቸውን የኢንቨስትመንት ማነቆ በመፍታት ወደ ሥራ እንዲገቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡

166. በኢንዱስትሪው የሚገኙ ባለሙያዎች አቅም ለማጎልበት እና ሥልጠናውን ውጤታማ ለማደረግ በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ከሥጋ፣ ወተትና መኖ ኢንዱስትሪ ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ

የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ውጤታቸውም መለካት የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

167. ኢንስቲትዩቱ የድጋፍ እና ክትትል ሥራውን ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ በነባር፣ ሥራ በጀመሩ እና በግንባታ ላይ ያሉ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ኢንዱስትሪዎችን የሥራ እንቅስቃሴ በመስክ በመከታተልና በየካምፓኒው ደረጃ እንዲጠናቀሩ በማማከር ኢንስቲትዩቱ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወር፣ ዘጠኝ ወር እና ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለከፍተኛ አመራሩ አቅርቦ ማስገምገም አለበት፡፡

168. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሐ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት ሊቋቋም ይገባል፡፡

169. በአጠቃላይ ኢንስቲትዩቱ የተሰጠው ተግባር እና ኃላፊነት በማቀነባበር (Processing) ሂደቱ ላይ ኢንዱስትሪዎችን መደገፍ ሲሆን በአሁኑ ወቅት የአቅርቦት (Production) ሂደቱ ላይ የሚሰራበት ሁኔታ ቢኖርም (ኢንስቲትዩቱ ለመኖ እና እንስሳት እርባታ 1.5 ሚሊዮን ብር በላይ በየዓመቱ መድቦ የሚንቀሳቀስ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት የታወቀ በመሆኑ፤) ኢንስቲትዩቱ የተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት በማቀነባበር ሂደቱ ላይ ትኩረት አድርጎ ሊሰራ ይገባል፡፡

170. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት በታዩ የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣ የሥጋ፣ ወተት እና መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች እና በከተማ መስተዳደር የሚገኙ የኢንዱስትሪ የሥራ ሂደቶች በኦዲቱ ወቅት የሚፈለጉ መረጃዎችን በሙሉ በማቅረብ እና ለቀረቡ ቃለ-መጠይቆች በወቅቱ መልስ በመስጠት ለተደረገልን ትብብር ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

አባሪ- 1

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች /Issues/ | የመገምገሚያ መስፈርት /Evaluative Criteria/ |
|---|---|
| 1. በሥጋና በወተት ኢንዱስትሪ ልማት ሥራ ላይ ለተሰማሩ አካላት መልማት የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርፀት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች በማሸጋገር ጥራቱንና ደረጃውን የጠበቀ ምርት ማምረት እንዲችሉ እገዛ መደረጉን እንዲሁም ምርቶቹን ለአገር ውስጥ እና በዓለም አቀፍ ገበያ ማቅረብ እንዲቻል የገበያ ጥናቶችን በማከናወን፣ በማስተዋወቅና በማስተሳሰር ድጋፍና ክትትል መደረጉን ማረጋገጥ፤ | |
| 1.1. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ሥራ ላይ ለተሰማሩ አካላት መልማት የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች በምርምርና ሥርፀት ተለይተው ወደ ኢንዱስትሪዎቹ እንዲሸጋገሩ ድጋፍ የተሰጠ መሆኑን መገምገም፤ | 1. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች በምርት ሂደት፣ በምርት ዕቅድና በጥራት ቁጥጥር ላይ ድጋፍና የማማከር አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፤ |
| | 2. ኢንስቲትዩቱ የወተት ማቀነባበሪያዎች እና የሥጋ ኢንዱስትሪዎችን በበቂ ባለሙያዎችና የላብራቶሪ ዕቃዎች ተደራጅተው ጥራቱና ደህንነቱ የተረጋገጠ የዓለም አቀፍ መስፈርትን ያሟላ ምርት ለሃገር ውስጥና ለዓለም ገበያ እንዲያቀርቡ ሊደገፍ እና ሰርተፊኬሽን እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፤ |
| | 3. በሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ለሚሠማሩ ባለሀብቶች በቴክኖሎጂ መረጣ፣ በድርድር፣ በግንባታ፣ በተከላና በሙከራ ምርት የምክር ድጋፍ መሰጠት አለበት፤ |
| | 4. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች ሊለሙ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን በምርምርና ሥርጸት በመለየት ወደ ኢንዱስትሪዎች በማሸጋገር ገበያ ውስጥ እንዲገቡ ሊደገፉ ይገባል፤ |
| | 5. ኢንዱስትሪዎቹ የምርምርና ሥርጸት ክፍሎች እንዲያቋቁሙ መደገፍ አለባቸው፤ |

| | |
|---|---|
| | 6. ኢንስቲትዩቱ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪዎች ታዳሽ የኃይል ምንጮችን እንዲጠቀሙና የአከባቢ ብክለት እንዳያስከትሉ ድጋፍ መሰጠት አለበት፤ |
| | 7. ኤክስፖርት ቄራዎች እና የወተት ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪዎች ደረጃውን የጠበቀ የሥጋና የወተት ማመላለሻ ኮልድ ትራክና ሪፍሪጅሬትድ ኮንቴነር እንዲኖራቸው እንዲሁም ወቅታዊ የቴክኒክ ፍተሻ የሚካሄድበት ሥርዓት እንዲዘረጋ ድጋፍ መደረግ አለበት፤ |
| | 8. የውጭ ባለሃብቶች በሥጋና በወተት ፕሮሴሲንግና ሬንደሪንግ በሰፊው እንዲሳተፉና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያደርጉ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በሂደት ልምድ የሚቀስሙበት ሁኔታ ሊመቻችላቸው ይገባል፤ |
| | 9. በወተትና የወተት ውጤቶች የተለያዩ እንደ ጥራት፣ የአሲዲቲ፣ የላክቶሜትር፣ የፕሮቲን ወዘተ የመሳሰሉ በርካታ ፍተሻዎች እንዲከናወኑ እገዛ ሊደረግ ይገባል፤ |
| | 10.የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ድጋፍ አሰጣጥ እና ቴክኖሎጂ አቅርቦት ባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (Cross Cutting Issues) ያካተቱ ሊሆኑ ይገባል፤ |
| | 11.በሥጋና ሥጋ ተረፈ ምርት ኢንዱስትሪዎች ወጪ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮችን በማስረጽ ምርትና ምርታማነት እንዲሁም የምርት ጥራት የሚሻሻልበት ስልት ሊቀየስና ሊተገበር ይገባል፤ |
| | 12.በኢንስቲትዩቱ የሥጋና ወተትን ኢንዱስትሪዎችን የሚመለከቱ ምርምር ሥራን ለማካሄድ በዕቅድ የተገዙ ንብረቶች/መሳሪያዎች እንዲሁም ኬሚካሎች በአግባቡ ሊያዙ፣ ለብክነት ሳይጋለጡ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ጊዜያቸው ያለፈባቸው /የማይሰሩት (Expired /damaged) የሆኑት የሚወገዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፤ |
| | 13.ኢንስቲትዩቱ በምርምር የተገኙና በተግባር ተፈትሸው ውጤት ያስገኙ የምርምር ውጤቶችንና አሰራር ሥርዓቶችን በመቀመር ለሌሎች በመስኩ ለተሰማሩ ኢንዱስትሪዎች ሥራዎች እንዲተላለፉ ሊያደርግና ተግባራዊነታቸውን ሊከታተል ይገባል፤ |
| | 14.ኢንስቲትዩቱ የመኖ ምርት ኢንዱስትሪዎችን እድገት መሠረት ያደረጉ ዘመኑ ያፈራቻውን ቴክኖሎጂዎች አገር ውስጥ እንዲላመዱ ምርምር በማከናወን ኢንዱስትሪዎችን ሊደግፍ ይገባል፤ |


| | |
|---|---|
| 1.2. **ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን የሚያሟሉ የእንስሳት ምርቶች ለውጭና ለአገር ውስጥ ገበያ በዓይነት፣ በጥራትና በብዛት ለማቅረብ የሚያስችሉ የገበያ ጥናቶች በማከናወን የማስተዋወቅና የማስተሳሰር ሥራ መሰራቱን ማረጋገጥ፤** | 15. የዳበረ ልምድ ካላቸው ሀገራት በሥጋ ብለታና እሽጋ፣ የሥጋ ፋብሪኬሽን ማሽኖች አጠቃቀም፣ በሥጋ ሎጅስቲክስ አመራር እና ግብይት ዙሪያ ኢንስቲትዩቱ ለኤክስፖርት ቄራዎች ድጋፍ ሊሰጥ ይገባል፤ |
| | 16. ኢንስቲትዩቱ ለእንስሳት ገበያ አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶች እንዲስፋፉ እንዲሁም ደረጃውን የጠበቀ የእንስሳትና የእንስሳት ምርት የማጓጓዣ ተሽከርካሪዎችና ሌሎች ፋሲሊቲዎች እንዲሟሉ ክትትል ማድረግ አለበት፤ |
| | 17. ለዘርፉ የግብዓቶች አቅርቦት በዓይነት በመጠን እና በጥራት አስተማማኝ እንዲሆን የግብዓት ኢንዱስትሪዎች እንዲለሙ ሊደግፍ፣ ከጥሬ ዕቃ አመራረት እስከ ዓለም አቀፍ ገበያ በምርቶች እሴት ሰንሰለት በዘርፉ ተዋናዮች መካከል ያለው ትስስር ውጤታማ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል ሊደረግ ይገባል፤ |
| | 18. በእንስሳት ምርቶች ላይ የንግድ ትርኢቶችና ባዛሮች ሊዘጋጁ ይገባል፤ |
| | 19. በገዥ ሀገራት በሚደረጉ የምርት ማስተዋወቂያ መድረኮች ላይ የእንስሳት ምርት ላኪዎች ምርቶቻቸውን እንዲያስተዋውቁ ሁኔታዎች ሊመቻቹላቸው ይገባል፤ |
| | 20. በእንስሳት ውጤቶች በመዳረሻ ሀገራት የሚፈለጉ አስገዳጅ መስፈርቶችን በመለየትና እንዲሟሉ በማድረግ ሊተዋወቁ ይገባል፤ |
| | 21. ኢንስቲትዩቱ ከውጭ ጉዳይ ሚ/ርና ኢምባሲዎች ጋር በመሆን አዳዲስ የሥጋ መዳረሻ ገበያዎች እና ነባር ገበያዎች ሊለይ እና ለኢንዱስትሪዎቹ ሊያስተዋውቅ ይገባል፤ |
| | 22. በወተት ማቀነባበር የተሰማሩ አካላት ለአገር ውስጥ ፍጆታ ብቻ ሳይሆን በኤክስፖርትና ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ወተት ለመተካት በሚያስችል (import substitution) ደረጃ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመቅረብ እንዲችሉ መደረግ አለበት፤ |
| | 23. ከውጭ የሚገቡ የእንስሳት ምርቶችን ለመተካት የሚያስችሉ ምርቶች በአገር ውስጥ በጥራትና በብዛት እንዲመረቱ ሊደረግ ይገባል፤ |
| 2. **የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ላይ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎች** | 24. በኢንስቲትዩቱ የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያስችሉ የፕሮጀክት ፕሮፋይሎች ሊዘጋጁና ሊሰራጩ እንዲሁም ወደ ዘርፉ ለሚገቡ ባለሀብቶች ጠቋሚ |


| | |
|---|---|
| መዘጋጀቱን፣ የደሰሳ ጥናት በማድረግና የመረጃ ቋት በመመስረት፣ መረጃዎችን በየጊዜው እየገመገሙ ወቅታዊ በማድረግ መረጃዎቹን ለሚፈልጉና ለሚመለከታቸው አካላት መሰራጨቱንና ተደራሽ የመረጃ ሥርዓት መመስረቱን እንዲሁም በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል መደረጉን መገምገም፤ | ጥናት ሊደረግና በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ ክትትል በማድረግ በአፈጻጸም ላይ ለሚከሰቱ ችግሮች መፍትሄ ሊሰጥ ይገባል፤ |
| | 25. ኢንስቲትዩቱ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን ሊያካሂድና በንዑስ ዘርፉ የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማነቆዎች ኢንዲወገዱ ድጋፍ መስጠት አለበት፤ |
| | 26. በወተት እና ሥጋ እንዲሁም መኖ እንዲስትሪ ምርቶች ፍላጎትና አቅርቦት ላይ ደሰሳ ጥናት ሊከናወን እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፤ |
| | 27. በስጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት መልካም ተሞክሮ ያላቸው ሃገራትና ካምፓኒዎች ተለይተው ተሞክሮዎቹ ተቀናብረው በኤክስፖርት ቄራዎችና ወተት ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች ተግባራዊ (implement) ሊደረጉ ይገባል፤ |
| | 28. የሥጋ መዳረሻ ገበያዎችን የሥጋ ፍላጎት፣ ዋጋና የተወዳዳሪ ሀገራት የምርት አቅርቦት ዙሪያ የደሰሳ ጥናቶችን በማድረግ መረጃዎችን በማጠናቀር ለኤክስፖርት ቄራዎች እንዲደርሳቸው ሊደረግ ይገባል፤ |
| | 29. ለሥጋና ወተት ኢንዱስትሪው ልማት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኖሎጂ፣ የገበያና ሌሎች መረጃዎች ሊሰበሰቡ፣ ሊተነተኑ እና ተደራጅተው ለተጠቃሚዎች ሊሰራጩ ይገባል፤ |
| | 30. ኢንስቲትዩቱ ለሥጋና ወተት ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የሚውሉ የኢንቨስትመንት ቦታዎች በዝርዝር ለይቶ እንዲታወቁ በማድረግ መረጃውን በዳታ ቤዝ በማጠናከር ላባለሃብቶች በቀላሉ መስጠት ይጠበቅበታል፤ |
| | 31. ኢንስቲትዩቱ ሥጋና ወተት ወደ ሚላኩባቸው መዳረሻ ገበያዎች እስኪደርሱ ድረስ ሱፐርቪዥን ሥራ በማድረግ ለቄራዎች ግብረ- መልስ በመስጠት የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበሩ ሊደረግ ይገባል፤ |
| | 32. የእንስሳት አቅርቦት (Supply Chain) ላይ የደሰሳ ጥናት በማካሄድ ለኢንዱስትሪዎቹ መረጃው ሊሰጣቸው ይገባል፤ |
| | 33. ኢንስቲትዩቱ ከክልሎችና ከኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር በመተባበር በእንስሳት ውጤቶች ማቀነባበር መሬት ወስደው ግንባታ ያልጀመሩ፣ ግንባታቸውን ጨርሰው ወደ ማምረት ያልገቡ ባለሃብቶችን በመለየት የኢንቨስትመንት ውሳኔዎች እንዲያገኙ ሊያደርግ ይገባል፤ |

| | |
|---|---|
| | 34. ኢንስቲትዩቱ በሀገሪቱ የሚገኙትን የክልሎች የወተት ሀብትና መኖ የማምረት አቅም እንዲሁም የእንስሳት አቅርቦት መጠን ሊለይና መረጃዎችን ሊያደራጅ ይገባል፤ |
| 3. የሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የድጋፍ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን መገምገም እንዲሁም ዘርፉን የሚያግዙና ተወዳዳሪ የሚያደርጉ የቴክኖሎጂ፣ የቴክኒክ፣ የግብይት፣ የሥራ አመራርና ሌሎች እንደአስፈላጊነቱ የሚዘጋጁ ተግባር ተኮር ሥልጠናዎችን በመስጠት ድጋፍ መደረጉን ማረጋገጥ፤ | 35. ኢንስቲትዩቱ በተለይም በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር ውጤታማ የምርት የቴክኖሎጂና የሥልጠና ትስስር እንዲኖራቸው በማድረግ ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ ማድረስ ይጠበቅበታል፤ |
| | 36. ወተትና የወተት ምርቶች ከሕዝብ ጤንነት አንጻር ትልቅ ትኩረት የሚሰጣቸው በመሆኑ በዘርፉ ልዩ ሥልጠና የወሰዱና በሃይ ቴክ መሣሪያዎች አጠቃቀም ክህሎት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲተገበር መደረግ አለበት፤ |
| | 37. በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሥልጠናዎች በዕቅድ ላይ የተመሰረቱ፣ ወቅታቸውን የጠበቁ እንዲሁም ውጤታቸውም መለካት የሚችሉ መሆን ይኖርባቸዋል፤ |
| | 38. ኢንስቲትዩቱ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ከሚገኙ የግልና የመንግሥት ተቋማት ጋር ትብብር ማድረግ እና በግል ተቋማት መካከልም ተመሳሳይ ትብብር እንዲደረግ ማበረታታት አለበት፤ |
| | 39. ኢንስቲትዩቱ የኢንዱስትሪ ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲሁም በዓለም ገበያ ለማስተዋወቅ ድጋፍ መስጠት፣ ውጤታማ የግብይት ሥርዓት እንዲዘረጋ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት አለበት፤ |
| | 40. ኢንስቲትዩቱ በዘርፉ የአገር ውስጥ ምርምር አቅም እንዲጠናከር እና የዘርፉን የዝቅተኛና መካከለኛ የሰው ኃይል ፍላጎት ለማሟላት ከኢንዱስትሪዎች፣ ዩኒቨርሲቲዎች እና ከቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፤ |
| | 41. ኢንስቲትዩቱ ከክልሎች ጋር ተከታታይ ግንኙነት እንዲኖረው በማድረግ ለባለሃብቶች ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት አዳዲስ ባለሃብቶች በዘርፉ በብዛት እንዲሰማሩ ማድረግ የሚቻልበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይገባል፤ |
| | 42. ኢንስቲትዩቱ ከግብርና ሚ/ር፣ ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፣ ክልሎችና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተቀናጀ አሰራር በማቋቋም አብሮ መሰራት አለበት፤ |

| | |
|---|---|
| | 43.ኢንስቲትዩቱ የኮልድ ቼይን ሰንሰለት ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ከቁራዎች፣ ከአየር መንገድ፣ ከኤርፖርቶች ድርጅትና ከትራንስፖርት ሚ/ር ጋር ቅንጅታዊ አሰራሮችን በመዘርጋት የመግባቢያ ሰነድ (MOU) መፈራረምና ተግባራዊ መደረግ ይኖርበታል፤ |
| | 44.በኢንስቲትዩቱ በሚገኙ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች መካከል ቅንጅታዊ አሰራር ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፤ |
| | 45.በነባር፣ ሥራ በጀመሩ እና በግንባታ ላይ ያሉ የሥጋ፣ የወተት እና የመኖ ኢንዱስትሪዎችን የሥራ እንቅስቃሴ በመስክ በመከታተልና በየካምፓኒው ደረጃ እንዲጠናቀሩ በማማከር ኢንስቲትዩቱ ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመት፣ የስድስት ወር፣ የዘጠኝ ወርና ዓመታዊ የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለከፍተኛ አመራሩ አቅርቦ ማስገመግም አለበት፤ |
| | 46.በኢንስቲትዩቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመገምገም፣ ለማማከር እና የአቅም ግንባታ መርሐ ግብሮች ላይ አስተያየት ለመስጠት የሚያስችል የአማካሪ ምክር ቤት ሊቋቋም ይገባል፤ |

**የአሰራር ሥርዓት መግለጫ** **አባሪ 2**






## አባሪ 3

**በኦዲቱ ወቅት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው እና የመስክ ዕይታ የተደረገባቸው አከባቢዎች ዝርዝር ማሳያ፡-**

| ተ/ቁ | የክልሉ ሥም | የሥጋና ወተት ማቀነባበሪያዎች | በናሙና የተመረጡ የከተማ የኢንዱስትሪ የሥራ ሂደቶች |
|---|---|---|---|
| 1 | ኦሮሚያ | ሄልሚክስ/ሃሽም ኤክስፖርት ቄራ | |
| 2 | ኦሮሚያ | ሉና ኤክስፖርት ቄራ | የሞጆ ከተማ አስተዳደር የኢንዱስትሪ የሥራ ሂደት |
| 3 | ኦሮሚያ | ኤልፎራ ኤክስፖርት ቄራ | |
| 4 | ሶማሌ | ጅግጅጋ ላይቭስቶክ ኤክስፖርት ቄራ | የጅግጅጋ ከተማ አስተዳደር የኢንዱስትሪ የሥራ ሂደት |
| 5 | ደቡብ | አልሚ ትኩስ ወተት ማቀነባበሪያ | የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር የኢንዱስትሪ የሥራ ሂደት |
| 6 | ኦሮሚያ | ሆላንድ ዴይሪ ወተት ማቀነባበሪያ | |
| 7 | ኦሮሚያ | ጀነሲስ ፋርም | |
| 8 | ኦሮሚያ | አደአ የህብረት ሥራ ማህበራት የወተት ማቀነባበሪያ | |
| 9 | ኦሮሚያ | ያቅላ የወተት ማቀነባበሪያ | |
| 10 | አዲስ አበባ | ኤሌምቱ የወተት ማቀነባበሪያ | |